# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 282 ሰኔ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም

- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ




# የቀዳማዊት እመቤት ጽሕፈት ቤት ያስገነባውን 23ኛ ትምህርት ቤት በሲዳማ ክልል አስመረቀ

### - ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሐዋሳና በወላይታ የተከናወኑ የልማት ሥራዎችን ጎብኝተዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የቀዳማዊት እመቤት ጽሕፈት ቤት ያስገነባውን 23ኛውን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሲዳማ ክልል አስመረቀ።

በሌላ በኩል ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሐዋሳና በወላይታ የተከናወኑ የዳቦና ዱቄት ፋብሪካ ግንባታዎች ፣ የመሰረተ ልማትና የግብርና ልማት ሥራዎችን ጎብኝተዋል።

የቀዳማዊት እመቤት ጽሕፈት ቤት በሲዳማ ክልል ሆኮ ወረዳ የተገነባው "ኦዲ ቦኮ" ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፣ ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው፣ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝና የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ደስታ ሌዳሞ ትናንትና መርቀዋል።

በወቅቱ ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ትምህርት የዕውቀት ሁሉ መሠረት በመሆኑ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ገበታ መላክ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

የአካባቢው ማህበረሰብ ከመንግሥት ጋር በመ ሆን ለትምህርት ቤቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማሟላት ትውልድ ተሻጋሪ እንዲሆን በጥንቃቄ መያዝ እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተደድር አቶ ደስታ ሌዳሞ በበኩላቸው፤ ትምህርት ቤቱ የተገነባበት ስፍራ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያልነበረበት በመሆኑ ትምህርት ፍለጋ ከአካባቢያቸው ርቀው የሚሄዱ ተማሪዎችን ችግር የሚያቃልል እንደሚሆን ገልጸዋል።

ትምህርት ቤቱ 12 የመማሪያ ክፍሎች፣ ሁለት

የቀዳማዊት እመቤት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# "ያለ ህዝብ ንቁ ተሳትፎ ከተማና ሀገር ማልማት አዳጋች ነው"

### - ድምጻዊት ፀደኒያ ገብረማርቆስ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ያለ ህዝብ ንቁ ተሳትፎ መንግሥት ብቻውን ከተማና ሀገር ማልማት አዳጋች ነው ስትል ድምጻዊት ፀደኒያ ገብረማርቆስ ተናገረች። ድምፃዊቷ መንግሥት የህዝብን ሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥና መልካም አስተዳደርን ማስፈን እንደሚጠበቅበትም አመለከታለች።

"ያለ ህዝብ ንቁ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የአማራ ባንክ ሁሉንም በእኩልነት በማገልገል በትብብር የሚሰራ የሁሉም ባንክ ነው

### - ባንኩ በመላ አገሪቱ 72 ቅርንጫፎችን በመክፈት በይፋ ሥራ ጀምሯል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የአማራ ባንክ ሁሉንም በእኩልነት በማገልገል በትብብር የሚሰራ የሁሉም ባንክ መሆኑን የባንኩ የቦርድ ሊቀመንበር አቶ መላኩ ፋንታ ገለጹ፡፡ ባንኩ በመላ አገሪቱ 72 ቅርንጫፎች በመክፈት ትናንት በይፋ ሥራ መጀመሩን አብስሯል፡፡

አማራ ባንክ የቦርድ ሊቀመንበር አቶ መላኩ ፋንታ ትናንት በባንኩ ዋና መስሪያ ቤት በተዘጋጀው የምረቃ ሥነ ሥርዓት በይፋ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር እንደገለጹት፤ አማራ ባንክ "ከባንክ ባሻገር" የሚል መሪ ቃል የያዘ ሁሉንም በእኩልነት በማቀፍ እና በትብብር የሚሰራ የሁሉም ባንክ ነው።ባንኩ ሥራ በመጀመሩ እንኳን ደስ አላችሁ ።

አማራ ባንክ ለአንድ ዓመት ከሦስት ወር ባደረገው

የአማራ ባንክ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- ገበበ ገብሬ



ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ

# ‹‹እኔ ከሚለው ይልቅ እኛ የሚለው ሀሳብ አሸናፊ ሲሆን ኢትዮጵያ የተሻለ ትጠቀማለች››

### - ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ አማረ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊት የድጋፍና ልማት ማህበር ፕሬዚዳንት

ገጽ 2







# ዜጎች በትምህርት ታንጸው እንዲያድጉ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን ቢሮው ገለጸ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ለትምህርት ሥራ ከምን ጊዜውም በላይ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት እና አመርቂ የሆኑ ድጋፎችን በማድረግ ዜጎች በትምህርት ታንጸው እንዲያድጉ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ገለጸ።

"የትምህርት ጥራትን በማረጋገጥ የብልጽግና ጉዟችንን በሳይንስ ፈጠራ ሥራ እውን እናደርጋለን" በሚል መሪ ሃሳብ ሲካሄድ የቆየው 7ኛው የሳይንስ ፈጠራ ሥራ ዐውደ ርዕይ በትናንትናው ዕለት ተጠናቋል።

በማጠናቀቂያ መርሐ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ እንደገለፁት፤ መንግሥት ለትምህርት ሥራ ከምጊዜውም በላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው። በአዲስ አበባ ከተማም ለትምህርት ሥራ አመርቂ የሆኑ ድጋፎችን በማድረግ የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች በተለያዩ ዘርፎች ተኮትኩተው እንዲያድጉ የበኩሉን ሚና እየተወጣ ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደው የተማሪዎችና የመምህራን የሳይንስ፣ ሒሳብ፣ ልዩፍላጎት፣ ሥዕልና ቅርፃቅርፅ ውድድር ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂ ዘርፍ ባለምጡቅ አዕምሮ ዜጎች ባለቤት መሆኗን ያየንበት ነው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው ሂደቱም ሕብረ ብሔራዊ አንድነት እና ወንድማማችነት የተንፀባረቀበት እንደነበረ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አድማሱ ገለጻ፤ የተጠናቀቀው 7ኛው የሳይንስና ፈጠራ ዐውደ ርዕይ ተማሪዎች እንደ ሀገር በቴክኖሎጂው ዘርፍ ለተያዘው ዕቅድና ለሀገር ብልፅግና መሠረቶች መሆናቸው የተረጋገጠበት ዐውደ ርዕይ ነው። መርሐ ግብሩ ለወደፊቱም ቀጣይነት ባለው መልኩ ይከናወናል ብለዋል።

በተለይ የሀገር ተረካቢው ትውልድ የሳይንስ ፈጠራ ክህሎቱን እንዲያሳድግ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን በመጠቆም፤ ባለፉት ቀናት ከተካሄዱት የሳይንስ ፈጠራ ውድድር፣ ጥናትና ምርምር፣ ውይይት እና ሌሎች መርሐ ግብሮች ከፍተኛ ልምድ መቀሰሙን ተናግረዋል።

በመርሐ ግብሩ በሒሳብ፣ ኬሚስትሪ፣ ባዮሎጂ፣ ፊዚክስ እና በልዩፍላጎት እንዲሁም በሥዕልና ቅርፃ ቅርፅ ፈጠራ ውድድር አሸናፊ የሆኑ ተማሪዎች መምህራንና አካል ጉዳተኞች ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

በማጠናቀቂያ መርሐ ግብሩ የተለያዩ ትርኢቶች፣ የኢትዮጵያን ብሔር ብሔረሰቦች አልባሳት እና ባህላዊ ጭፈራዎችን የሚያሳዩ ፕሮግራሞች ከየክፍለ ከተማው በተውጣጡ ተማሪዎች ቀርቧል።



አቶ አድማሱ ደቻሳ

# በህፃናትና ሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለመቀነስ ሁሉም ዜጋ የበኩሉን እንዲወጣ ጥሪ ቀረበ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በህፃናትና ሴቶች ላይ የሚደርሱ ዘርፈ ብዙ ጥቃቶችን ለመቀነስ ሁሉም ዜጋ የበኩሉን እንዲወጣ የአዲስ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ጥሪ አቀረበ፡፡

በኢትዮጵያ ለ31ኛ ጊዜ የተከበረው የህፃናት ቀን "ህፃናት ላይ የሚፈጸም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ይቁም" በሚል መሪ ሃሳብ ተከብሯል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሃና የሺንጉስ እንደገለጹት፤ በመዲናዋ በህፃናትና ሴቶች ላይ የሚደርሱ ዘርፈ ብዙ ጥቃቶች ይስተዋላሉ፡፡ እነዚህን ጥቃቶች ለማስቀረት እያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅ ኃላፊነት መወጣት ይኖርበታል።

ጥቃቶቹን ለማስቀረት ማህበረሰቡን በህፃናትና ሴቶች ዙሪያ ያለውን አመለካከትና ልማድ ለመቀየር የሚያስችል ሥራ ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ሃና፤ ቢሮው በግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር ሃና ገለጻ፤ ህፃናትና ሴቶች የማህበራዊ ጥበቃ ሽፋን በመስጠት ከድህነት ስጋት እንዲወጡ ማድረግ ከጥቃት እራሳቸውን እንዲጠብቁ ያግዛል። ለዚህም በህፃናትና መብት፣ ደህንነትና ድጋፍ ዙሪያ መጠነ ሰፊ ሥራ ይጠይቃል።

ቢሮውም የሴቶችና ህጻናትን ጥቃት ለማቃለል ከተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦች ጋር የሚያከናውናቸውን የትብብር ሥራዎች አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።


በቢሮው የህፃናት መብት፣ ደህንነት፣ ድጋፍና ክብካቤ ዳይሬክተር አቶ አንዱዓለም ታፈሰ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በመዲናዋ ህፃናትና ሴቶችን ከጥቃት ለመጠበቅ በሚከናወኑ ሥራዎች ላይ የተለያዩ የአተገባበር ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡

ችግሮቹን ደረጃ በደረጃ ከመፍታት ጎን ለጎን በከፋ ድህነት፣ የመብት ጥሰት፣ የድህንነት ችግር ውስጥ የሚኖሩ ህፃናትና ሴቶች አስፈላጊው ጥበቃ እንዲያገኙና መብታቸው ተከብሮ እንዲኖሩ ለማድረግ የሁሉንም ዜጋ ድጋፍ ያስፈልጋል ብለዋል።

ህፃናትና ሴቶች በማህበራዊ ሕይወታቸው ለተለያዩ አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተጋላጭነት በመሆናቸው የህብረተሰቡ ግንዛቤ በማሳደግ የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓትን መጠናከር አለበትም ሲሉ ዳይሬክተሩ



ዶክተር ሃና የሺንጉስ



አቶ አንዱዓለም ታፈሰ

ተናግረዋል፡፡

የህጻናትና ሴቶች ጥቃት በተመለከተ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለውን አነስተኛ ግንዛቤ በማሳደግና ጥፋቶች ሲገኙም የእርምት ዕርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ ቢሮው የተለያዩ ሥራዎች እያከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ ይሁንና አሁንም በየአካባቢው የተለያዩ ጥቃቶች ስለሚከሰቱ ሁሉም ዜጋ የሚጠበቅበትን ሚና ሊወጣ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ሁሉም ዜጋ በህፃናትና ሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ድርጊቶችን መታገስ እንደሌለበት ገልጸው፣ ማህበረሰቡ የህፃናትና ሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ተግባራትን አጥብቆ መቃወምና ሲፈጸሙ ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ‹‹እኔ ከሚለው ይልቅ እኛ የሚለው ሀሳብ አሸናፊ ሲሆን ኢትዮጵያ የተሻለ ትጠቀማለች››

**- ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ አማረ**
**የቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊት የድጋፍና ልማት ማህበር ፕሬዚዳንት**

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- እኔ ከሚለው አስተሳሰብ ይልቅ እኛ የሚለው ሀሳብ አሸናፊ ሲሆን ኢትዮጵያም እንደአገር የተሻለ ተጠቃሚ ትሆናለች ሲሉ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊት የድጋፍና ልማት ማህበር ፕሬዚዳንት የሃምሳ አለቃ ብርሃኑ አማረ ገለጹ።

የኢትዮጵያ ሠራዊት የድጋፍና ልማት ማህበር አስቸኳይ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤውን ትናንት አካሂዷል።

በወቅቱ የሃምሳ አለቃ ብርሃኑ አማረ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዛሬ ላይ እንደ አገር እኔ ብቻ የሚለው ሀሳብ ገዝፎ እኛ የሚለውን ሀሳብ ውጦታል።

አገር የምትገነባው ደግሞ እኛ በሚል የጋራ እሳቤ ስለሆነ ከእኔ ይልቅ እኛ የሚል ሀሳብ አሸናፊ ሲሆን ኢትዮጵያ እንደሀገር ተጠቃሚ እንደምትሆን ትውልዱ መገንዘብ ይገባዋል ሲሉ ተናግረዋል።

የማህበሩ አባላት ወታደሮች በመሆናችንና በአገር ፍቅር ስሜት ስላደግን የአገር ጉዳይ ሁሌም ያሳስበናል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ አገር አገልግሎታችንን በፈለገች ጊዜ ግንባር በመዝመትም ሆነ በማሰልጠኛ ጣቢያዎች በመገኘት ልምዳችንን ያለ ስስት አካፍለናል።

በአገራችን ያለው ትልቁ ችግር የተግባቦት ችግር መሆኑን ያመለከቱት ፕሬዚዳንቱ፤ ሁሉም ነገር ሚሳካው የአገር ሕልውና ሲረጋገጥ በመሆኑ እኔ ያልኩት ከሚል እሳቤ በመውጣት የሌሎችን ሀሳብ ለማዳመጥ መዘጋጀትና አንድነትን ማጠናከር እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ከአንድነት ይልቅ ልዩነት ላይ ትኩረት ተደርጎ በተሠራው ሥራ ወጣቱ አገሩን በአግባቡ እንዳይረዳ ተደርጎ መቆየቱን አስታውሰው፤ ወጣቱ ግን አገር ችግር ላይ በምትሆንበት ወቅት እኔ ብቻ ከሚል ስሜት ወጥቶ ያሳየው አንድነትና የከፈለው መስዋዕትነት ኢትዮጵያ ሁሌም በልጆቿ እንደማታፍር ያሳየና ትውልዱም የአባቶቹን ታሪክ እንዲጋራ ያደረገ ነው ብለዋል።

በቀጣይም ወጣቱም ለአገሩ ያለው ተቆርቋሪነት ከፍ እንዲልና አንድነቱን እንዲያጠናከር ታሪኩን በአግባቡ እንዲረዳ መሥራት ይገባል። ይህም የእኛነትን ስሜት ለማሳደግና በጋራ ለመልማት ያለንን አቅም ያሳድገዋል ሲሉ ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ እንደ አገር እንድትቀጥል ሁላችንም



ፎቶ፡ በአዩብ ተፈሪ

ፍላጎታችንን በማቻቻል ሕመማችንና ቁስላችንን በተባበረ መንፈስ በማከም የአገር አንድነትና የክብር ከፍ እንዲል ከመንግሥት ጎን በመሰለፍ የበኩላችንን ድርሻ እንወጣለን ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሠራዊት የድጋፍና ልማት ማህበር የቀድሞው ሠራዊት አባላት ጡረታ እንዲከበርላቸውና ነጻ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ጥያቄ ማቅረቡን ጠቁመው፤ አገሪቱ ካለችበት ችግር አንጻር እስካሁን ምለሽ ባያገኝም እኔ ብቻ ሳይሆን እኛ የሚለውን ስሜት በመያዝ መፍትሄዎች በሂደት እንዲገኙ ጥረት እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንዲጠናከርና አገር በሁለት እግሯ ቆማ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ማህበሩ ከመንግሥት ጋር በትብብር ይሠራል ብለዋል።

ማህበሩ በአቅሙ ልክ ለአገር ማበርከት የሚችለውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት መንግሥት ባለው አቅም ሁሉ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

የኢትዮጵያ ሠራዊት የድጋፍና ልማት ማህበር ዓመታዊ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤውን በትናንትናው ዕለት ሲያካሂድ፤ በአገሪቱ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይና ማህበሩ ከምስረታ እስከ አሁን ያደረገውን ጉዞና ያስተናገዳቸው ተግዳሮቶች ላይ ምክክር ተደርጓል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መከፋፈላችን የፈጠረው የአቅም ብክነት

በአጭር ይሁን በረጅም፤ በቅርብ ይሁን በሩቅ ታሪኩ በፈተና ውስጥ ያላለፈ ሀገርና ሕዝብ የለም። በችግር ውስጥ ማለፍ ተፈጥሯዊ የሕይወት ኡደት አካል ነው። ትልቁና ዋነኛው ነገር ይህንን ፈተና በጽናት መሻገር የሚያስችል አቅምና ቁርጠኝነት መፍጠር ነው። ለዚህ ደግሞ የአንድ ሀገር ሕዝብ የተዋቀረበት የሥነ ልቦና ውቅር ወሳኝ ነው።

ችግሩ ይዞት በመጣው ተግዳሮቶች ላይ አይንን ተክሎ በተስፋ መቁረጥ ከመቆዘም ይልቅ ችግሩ ይዞ የመጣውን መልካም አጋጣሚ በጥንቃቄ መመልከት፤ ችግሩን ከመተንተንና ከመዘርዘር ወጥቶ አቅምን አስተባብሮ ለመፍትሄ መስራትን የሚጠይቅ ነው።

በዓለም የቅርብ ታሪክ ውስጥ በብዙ ፈተና ውስጥ ያለፉ ሀገራት ተጨባጭ እውነታም የሚያሳየው ይህንኑ ነው። ጀርመን፣ ጣሊያን እና ጃፓን መሪዎቻቸው በሄዱበት የጥፋት መንገድ የተነሳ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ምክንያት ያጋጠማቸው ፈተና የአደባባይ ምስጢር ነው። በዚህም የሀገራቱ ሕዝቦች እጅግ ከባድ ዋጋ ከፍለዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ጠንካራ የተባለ ኢኮኖሚያቸው ተንኮታኩቶ እንደሀገር መጽናት የሚያስችላቸውን አቅም አጥተው፤ ከተሞቻቸው የድንጋይ ክምር ሆነው፤ ሕዝባቸው ለአጽናኝ በሚከብድ ብሄራዊ ኀዘን ውስጥ ለመቆየት ተገደው ነበር። ዓለምም ስለነሱ ውድቀት ከፍ ባለ ድምጽ ሲያወራ ድምፁን ላለመስማት የሚችሉበት እንጥፍጣፊ ብርታት አልነበራቸውም።

በዚያ የፈተና ወቅት ሀገራቱ ከገቡበት ፈተና ለመውጣት የረዳቸው ቀደም ባለው ዘመን እንደ ሕዝብ የገነቡት ጠንካራ የሥነ ልቦና ውቅር እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል። ይህ የሥነ ልቦና ውቅር ከችግሮቻቸው ይልቅ ችግሮቻቸውን አሸንፈው ለመውጣት የሚያስችላቸውን ብሄራዊ አቅም መገንባት አስችሏቸዋል።

ከችግሮቻቸው በላይ ሆነው እንዲያስቡና ያሰቡትን እንዲፈጽሙም ረድቷቸዋል። የገቡበት ችግር የፈጠረውን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ማገገም፤ ከዚያም አልፈው ከፍ ባለ ስገነት ላይ መቆም ችለዋል። ከቁዘማና አንገት ከመድፋት ወጥተው ቀና ብለው መራመድ የሚችሉበትን ብሄራዊ አቅም ገንብተዋል።

ይህ እንደ ሀገር ከችግሮች በላይ ሆኖ የማሰብ እና የመፈፀም የሀገራት ተሞክሮ እኛ ዛሬ ላይ ካለንበት ብሄራዊ ፈተና በስኬት ለመሻገር ወሳኝ የሆነ የአቅም ምንጭ እንደሚሆን፤ በተለይም እኛ ኢትዮጵያውያን በቀደሙት ዘመናት ያካበትናቸው ብሄራዊ እሴቶችችን ለዚህ አቅም ግንባታ ጥሩ ግብዓቶች እንደሚሆኑ ይታመናል።

ለችግሮች ፈጥኖ እጅ አለመስጠት፤ በችግር ወቅት ተረዳድቶ ችግርን የመሻገር እንዲሁም ችግሮችን ከብሄራዊ ክብር ጋር አስተሳስሮ በችግሮች ላይ የመጨከን የቆየ ባህላችንን ሕይወት ልንዘራበት ይገባል። ችግሮች ይዘውት በመጡት ፈተና ላይ ዓይንን ተክሎ በተስፋ መቁረጥ ከመቆዘም ይልቅ ችግሩ ይዞ የመጣውን መልካም አጋጣሚ በማስተዋል መመልከት እንዲሁም ችግሩን ከመተንተንና ከመዘርዘር ወጥቶ አቅምን አስተባብሮ ለመፍትሄው መስራትን ይጠይቃል።

ሀገር እንደ ሀገር ፈተና ውስጥ በምትወድቅበት ወቅት ፈተናውን ተሻግሮ ለማለፍ የሚደረጉ ሁለንተናዊ ጥረቶች የመላውን ሕዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚጠይቁ፤ ከመንደርተኝነት አስተሳሰብ፣ ከዘር እና ከሃይማኖት የልዩነት ትርክት ወጥቶ በጋራ ሀገርን እንደ ሀገር የመታደግ የአስተሳሰብ መሰረት ላይ መቆምን የሚጠይቅ ነው።

ከተራ የፖለቲካ ትርፍና ውዳሴ ወጣ ብሎ ስለ ሀገርና የሀገር ክብር ማሰብን እና ለዚህ አስተሳሰብ መገዛትን፤ ራስንና የራስ የሆነውን ነገር ሁሉ ለሀገርና ለሕዝብ ክብር አሳልፎ መስጠትን ይጠይቃል። ይህንን ክብር በትውልዶች መካከል ደምቆ የማየት መሻትንም ጭምር ያካተተ ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን ወደ ራሳችን መመለስ ከቻልን አሁን ያጋጠሙን ችግሮች ከእኛ አቅም በላይ አይደሉም፤ መቼም ቢሆን ከአቅማችን በላይ ሊሆኑም አይችሉም። ከአቅማችን በላይ የሆኑ ያህል ያደረጋቸው መከፋፈላችንና ይኸው መከፋፈላችን የፈጠረው የአቅም ብክነት ነው። ከዚህ ብክነት ፈጥነን ከወጣን የነገይቱ ሀገራችን ባለ ብሩህ ተስፋ እንደምትሆን ለማሰብ የሚከብድ አይሆንም።




# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ብረትን መቀጥቀጥ እንደጋለ ነው

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያን እግር ኳስ ከዳር እስከ ዳር ያነቃቃና ሕዝቦቿንም ያስፈነጠዘው የድል ስሜት አሁንም አልበረደም። ብርቅዬዎቹ ዋልያዎች በአገራቸው ዓለም አቀፍ ጨዋታን ማድረግ የሚያስችል ስቴድየም በማጣታቸው ወደ ገለልተኛ አገር ማላዊ ተሰደው ጣፋጩን ድል ይዘው ተመልሰዋል። ዋልያዎቹ ከስልሳ ዓመት በኋላ የአፍሪካ እግር ኳስ ሃያሏን አገር ግብጽን ማሸነፋቸው ከስፖርት የበለጠ ብዙ ትርጉም እንዳለው ተደጋግሞ ተነግሯል። ሌላው ይቆየንና የዋልያዎቹ ድል በፖለቲካዊ ጉዳዮች ተከፋፍሎ በማሕበራዊ ገጾች ላይ ሲሻኮት ዘወትር የምናስተውለውን ማሕበረሰብ አንድ አድርጎ ማሳየቱ ለእግር ኳስ ስፖርታዊ ትርጉም ብቻ እንዳንሰጠው አድርጓል።

ዋልያዎቹ ለዘመናት ዝቅ ተደርገው ከሚታዩበት ደረጃ ወደ ከፍታው ተመልሰዋል። በዚህም ሕዝብ ተደስቷል፣ ኮርቷልም። ታዲያ ዋልያዎቹ በዚህ ደረጃ የሕዝብን ስሜት መግዛት ከቻሉና ልዩነቶቻችንን ወደ አንድነት የማምጣት ሃይል ካላቸው ከወጡበት ከፍታ እንዳይንሸራተቱ ምን ይደረግ? የሚለው ጉዳይ የሁሉም የቤት ስራ መሆን አለበት። ለዚህም ብዙ መስተካከል ካለባቸው አስተዳደራዊ ዝርዝር ነጥቦች ውስጥ አንኳሮቹን መጠቆም ወይም ማስታወስ ተገቢ ነው። ይህ የዋልያዎቹ ልብን የሚያሞቅና የሁሉም ኩራት የሆነ ድል ነገም እንዲቀጥል ከአሰልጣኝ ውበቱ አባተ ጀምሮ በፌዴሬሽን በኩል ከወዲሁ ዝርዝር እቅዶችን አውጥቶ መዘጋጀት ቀዳሚ ጉዳይ በመሆኑ ለስፖርቱ መሪዎችና ባለሙያዎች ትተነው መንግሥትንና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ትኩረት እናድርግ።

የዋልያዎቹና ፈርኦኖቹ ፍጥጫ አሁንም አላበቃም። በቀጣይ መስከረም ላይ የመልሱ ጨዋታ በካይሮ ይደረጋል። ዋልያዎቹ ታሪክ በቀየሩበት ጨዋታ አስደንጋጭ ሽንፈት የገጠማቸው ፈርኦኖቹ ከደረሰባቸው ትችት(ውግዘት ማለት ይቀላል) አገግመው ሕዝባቸውን በተሻለ ድል ለመካስና ዋልያዎቹን ለመበቀል ያንን ቀን እንደሚጠብቁ እርግጥ ነው። ለዚህ ዋልያዎቹም ከወዲሁ በሥነልቦናም በአካል ብቃትና ቴክኒካዊ ጉዳዮች ራሳቸውን ማዘጋጀት እንዳለባቸው ይጠፋቸዋል ተብሎ አይታሰብም። የአሁኑ ድል አንዴ ተመዝግቧል፣ታሪክም ያስታውሰዋል። የበለጠ ትርጉም ያለው ድል እንዲሆን ግን ስለመልሱ ጨዋታም ማሰብ ያስፈልጋል። ዋልያዎቹ ከየትኛውም የአፍሪካ ብሔራዊ ቡድን ያነሰ አቅም እንደሌላቸው አሳይተዋል።

በእርግጥ ከዚህ ቀደም በተለይም ባለፈው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታ እንደ ኮትዲቯር ያሉ ግዙፍ ቡድኖችን በማሸነፍ ብልጭ ብሎ ሳናጣጥመው የሚጠፋ ተስፋ አሳይተውናል። ነገር ግን ቀጣይነት አልነበረውም።ለምን? ይህን በአግባቡ አጢኖ ዋልያዎቹ ፈርኦኖቹን በረቱበት ጨዋታ የነበራቸውን በውጤት የታጀበ አቅም እንዴት በቀጣይ ጨዋታዎች መድገም ይቻላል? የሚለውን ጉዳይ የአሰልጣኝ ቡድን አባላትና የቴክኒክ ኮሚቴው ጊዜ ወስዶ ሊመለከተው ቢችልም ከእግር ኳሳዊ ምክኒያቶች በበለጠ እገዛ የሚሹባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ ፌዴሬሽኑ የተሻሉ ከሚባሉ ብሔራዊ ቡድኖች ጋር ዋልያዎቹ በርካታ የወዳጅነት ጨዋታዎችን በማድረግ አቋማቸውን እየፈተሹ በጎደለው የሚሞሉበትን፣ የተጣመመውን የሚያቀኑበትን እድል መፍጠር ለነገ የሚለው የቤት ስራ አይደለም፡፡ ይህን ለማድረግ ግን በተለያዩ መንገዶች እገዛ እንደሚፈልግ ሚስጥር አይደለም፡፡

ፌዴሬሽኑ ዋልያዎቹ ከሜዳቸው ውጪ ጨዋታዎችን ለማድረግ በመገደዳቸው በአንድ ጨዋታ ለሜዳ ኪራይና ለመሳሰሉት ብቻ እስከ ሃምሳ ሺ ዶላር ወጪ እንደሚያደርግ ባለፈው መግለጫው ጠቁሞ ነበር። ይህም ካለው አቅም አንጻር ብዙ እንደማያራምደውና ጨዋታዎችን ከአገር ውጪ ሄዶ ማድረግ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደሚሳነው ስጋቱን ገልጾ ነበር። ይህ ዋልያዎቹና በአጠቃላይ የኢትዮጵያ እግር ኳስ በተነቃቃበት በዚህ ወቅት በሕዝብ ስሜት ላይ ውሃ ሊከልስ የሚችል አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ነገ ዋልያዎቹ በዚህ መነቃቃት ላይ ወደ አፍሪካ ዋንጫ የማምራት እድላቸው እየሰፋ ሲሄድ ይሄ አይነቱ እንቅፋት ሊያሳስብ አይገባም። መንግሥትም ይሁን የሚመለከተው አካልና ባለሀብቶች ድሎች ሲመዘገቡ ጮቤ ከመርገጥና ጊዜያዊ ሽልማቶችን ከማዥጎድጎድ በዘለለ ስለ ዋልያዎቹ ቀጣይ መንገድና እጣፋንታ በማሰብ እጃቸውን ወደ ኪሳቸው የሚሰዱበት ትክክለኛው ጊዜ አሁን ነው፡፡

ይህን የፋይናንስ ጉዳይ እንቅፋት እንዲሆን ካደረጉ ምክንያቶች ዋነኛው ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ጨዋታዎችን በሜዳዋ የሚያስተናግድ ስቴድየም አለመኖሩ ነው። ከዚህ ቀደም ይህ የስቴድየም ችግር ሲነሳ «ለየትኛው እግር ኳስ ነው» የሚሉ ምላሾች ከተለያዩ ወገኖች ሲሰጡ ማየት የተለመደ ነው። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም ከወራት በፊት የፓርላማ ንግግራቸው ላይ በስቴድየሞች ዙሪያ በሰጡት ምላሽ «መጀመሪያ ሰርታችሁ የተሻለ ነገር አሳዩ፣ አፍሪካ ዋንጫና ኦሊምፒክ ላይ ደጋግማችሁ በመሳተፍ ውጤት አሳዩን» በማለት መናገራቸው ይታወሳል። እርግጥ ነው መንግሥት ደረጃቸውን የጠበቁ ስቴድየሞች እንዲኖሩ ትኩረት ለመስጠት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያሉትን ማሳያዎች ይፈልግ ይሆናል። አዳዲስ የካፍና የፊፋን መስፈርት የሚያሟሉ ስቴድየሞችን ለመገንባት ብቻም ሳይሆን ተጀምረው ሳይጠናቀቁ ቆመው የቀሩትን ለማጠናቀቅም ቢሆን ገፊ ምክንያት ይፈልግ ይሆናል።

ዋልያዎቹ በፈርኦኖቹ ላይ የተቀዳጁት ይህ ታሪካዊ ድል ለዚህ በቂ ነው ማለት ባይቻልም የመንግሥትን አንጀት ለማራራት አያንስም። በዚህ ላይ እነዚህ ተጀምረው መጠናቀቅ የተሳናቸው ስቴድየሞች አገር በሌላት የውጭ ምንዛሬ ከመቀነቷ ፈታ፣ ሌሎች ሕዝብን ሊጠቅሙ የሚችሉ መሰረተ ልማቶች ከሚገነቡበት በጀት ቀንሳ የጀመረቻቸው በመሆኑ ዝምብሎ መመልከት እንደማይቻል ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ይህን የተጀመረ መነቃቃት አስቀጥሎ ዋልያዎቹን በቀጣዩ የአፍሪካ ዋንጫ ዳግም ለመመልከት «ብረትን እንደጋለ መቀጥቀጥ» ነውና ነገሩ ሌላው ቢቀር አንድ ስቴድየም እንኳን ቢሆን ርብርብ ተደርጎበት ለመጨረሻዎቹ የማጣሪያ ጨዋታዎች ዋልያዎቹ ከስደት እንዲድኑ ግፊት ማድረግ ይገባል፡፡

እርግጥ ነው መንግሥት አሁን ያለበት የውጭ ምንዛሬ እጥረት ይታወቃል። አብዛኞቹ የተጀመሩ ስቴድየሞችም አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቸው እንዲጠናቀቁ ቀላል የማይባል የውጭ ምንዛሬ ይፈልጋሉ። ለዚህ ግን ከታሰበበት መላ አይጠፋም። የመንግሥት ካዝና ቢነጥፍ በአገር ውስጥም ይሁን ባህርማዶ ለዋልያዎቹ የሚንሰፈሰፍ የእግር ኳስ ስሜት ያላቸው በርካታ ባለሀብት የስፖርት ቤተሰቦች ወደ ኪሳቸው እንዲገቡ ማስተባበር አንዱ መንገድ ሊሆን ይችላል። በትናንሽ ድሎች ሳይቀር ጮቤ የሚረግጡ ተራ የእግር ኳስ አፍቃሪዎችም ቢሆኑ ለዋልያዎቹ ከገንዘብም ያለፈ መስዋእትነት ለመክፈል ችላ እንደማይሉ እዚህ ጋር ማስታወስ ተገቢ ነው። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብም ይህ የድል ስሜት ሳይበርድ የሚያስተባብረው ካገኘ ለዋልያዎቹ የሚሰስተው ነገር አይኖርምና ይታሰብበት።

# ፓርቲው ለአብርሆት ቤተ-መጻሕፍት የሚያደርገውን ልገሳ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- አብርሆት ቤተ-መጻሕፍትን ለማደራጀት በሚደረገው ጥረት የመጻሕፍት ልገሳውን አጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዲስ አበባ ብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

የፓርቲው ጽህፈት ቤት በመጀመሪያ ዙር ያሰባሰባቸውን አምስት ሺህ 911 መጻሕፍት ትናንትና ለአብርሆት ቤተ-መጻሕፍት አስረክቧል።

የአዲስ አበባ ብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የድርጅት ጉዳይ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ይመር ከበደ መጻሕፍቱን ሲያስረክቡ፤ ትውልድ የሚያንጹ መጻሕፍትን ለአብርሆት ለማሰባሰብ የሚደረገውን ጥረት ሳይቋረጥ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

ከአንድ ባነሰ ጊዜ ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ መጻሕፍት ማሰባሰብ መቻሉን ጠቁመው፤ መጻሕፍቱ የሳይንስ፣ የፍልስፍናና ሌሎች ዘውጎችን ያካተቱ መሆናቸውን አንስተዋል።

በቀጣይም ተጨማሪ መጻሕፍትን ለማሰባሰብ ዘመቻ በማካሄድ የሁሉም ክፍለ ከተማ አመራሮችና የፓርቲው አባላት በስፋት እንዲሳተፉበት ይደረጋል ያሉት አቶ ይመር፤ ፓርቲው ከፍተኛ መጠን ያላቸውንና ትውልድ መቅረጽ የሚችሉ የንባብ ውጤቶችን ለማሰባሰብ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንደሚሰራ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ይመር ከሆነ፤ መጻሕፍትን ማሰባሰብና ማንበብ እንደአገርም ትልቅ ሀብት መፍጠር ነው። በዚህ ረገድ አብርሆት አገራዊ ሃብት የምናሰባስብበት ማዕከል እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይገባል።

በየዕለቱ የሚሰባሰቡ መጻሕፍትንም መጠቀም ከትውልዱ እንደሚጠበቅ አቶ ይመር ጠቁመው፤ መጽሐፍ አገርን መለወጥ እንደሚችል ጃፓን ጥሩ ምሳሌ ነች። በዚህ ረገድ ትውልዱ የንባብ ባህሉን በማሳደግ ለሀገር የሚጠቅም ሥራ ማከናወን ይገባዋል ብለዋል።

ጥንት አባቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን ጽፈው ያስቀመጧቸው፤ በሕክምና፣ በፍልስፍና ዘዴዎችና በሌሎች ዘርፎች በርካታ ጥንታዊ መጻሕፍት አሉን። እነዚህን ተጠብቀው የሚገኙ መጻሕፍትን ንቁ ትውልድ አውጥቶ ለአገር ጥቅም ሊያውላቸው ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው መጻሕፍቱን ሲረከቡ እንደገለጹት፤ የፓርቲው ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አባላትና አመራሮቹን አስተባብሮ መጻሕፍትን በማበርከቱ ምስጋና አቅርበዋል።

በመደጋገፍ አገር መለወጥ ይቻላል፤ በዚህ ረገድ ብልጽግና ፓርቲ ቅድሚያ ለሰው ልጅ አዕምሮ ዕድገት ሰጥቶ የንባብ ውጤቶችን ማበርከቱ አስተሳሰቡ ላይ እንደሚሰራ ማሳያ ነው ብለዋል።

አብርሆት የመጻሕፍት መዳረሻ ማዕከል መሆኑን የተናገሩት ዶክተር ሒሩት፤ ቤተመጻሕፍቱን ከማደራጀት ባለፈ በተለያዩ ክልሎች አላማውን የማጠናከር ግን ያለው ፕሮጀክት በመሆኑ ድጋፎቹ ቀጣይነት እንዲኖራቸውም ጥሪ አቅርበዋል።



አቶ ይመር ከበደና ዶክተር ሒሩት ካሳው

## የቀዳማዊት እመቤት ጽሕፈት ቤት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የላብራቶሪ ክፍልና አንድ ላይብረሪ ያለው ሲሆን 11 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎበታል።

የቀዳማዊት እመቤት ጽሕፈት ቤት በሀገር አቀፍ ደረጃ በሁለተኛ ዙር ካስገነባቸው 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ይሄኛው ለምርቃት ሲበቃ ሦስተኛው መሆኑ ታውቋል።

በተያያዘ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው በሀዋሳ ከተማ እየተገነባ ያለውን የዳቦና ዱቄት ፋብሪካ ትናንትና ጎብኝተዋል።

የሀዋሳ ዳቦና ዱቄት ፋብሪካ እየተገነባ ያለው በቀዳማዊት እመቤት ጽህፈት ቤት ሲሆን፣ የግንባታ ሂደቱን የተመለከቱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የዳቦ ፋብሪካው የግንባታ ሂደት መገምገማቸውንም በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው አስታውቀዋል።

በተመሳሳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ከትናንት በስቲያ በቀዳማዊት እመቤት ጽሕፈት ቤት በወላይታ ሶዶ ከተማ ከ55 ሚሊዮን ብር በላይ በመገንባት ላይ ያለውንና አፈጻጸሙ 67 በመቶ የደረሰውን የዳቦና ዱቄት ማምረቻ ፋብሪካ መጎብኘታቸው ይታወሳል።

ዶክተር ዐቢይ የፋብሪካው የግንባታ አፈጻጸም እንዲፋጠን አቅጣጫ ሰጥተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ልዑካቸው የጎበኟቸውና በግንባታ ሂደት ላይ ያሉት የዳቦ ፋብሪካዎች፣ በቀዳማዊት እመቤት ጽሕፈት ቤት በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተገነቡ ካሉ 10 የዳቦ ፋብሪካዎች መካከል መሆናቸው ተገልጿል።

ከፋብሪካ ጉብኝቱ ባለፈ ከከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጋር ግንባታ ላይ ያለውን የወላይታ ሶዶ አየር ማሪፊያን ጨምሮ በብላቴ እርሻ ልማትና አካባቢው እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሥራዎችን ጎብኝተዋል።

በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምርታመነትን የማሳደግ ግባችንን ለማሳካት የግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንት ወሳኝ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በወላይታ ሶዶ በግሉ ዘርፍ በ1 ሺህ 250 ሔክታር መሬት ላይ እየተከናወነ ያለውን የፍራፍሬ ምርት ውጤት የሚደነቅ መሆኑንም ገልጸዋል።

ቦታው ለዘመናት የነበረ ቢሆንም አልተጠቀምንበትም ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ ይህን አሰራር በመቀየስ የሙዝ፣ አቮካዶ ፣ ብርቱካንና ፓፓያ ምርቶችን በ11 ወራት ማዘጋጀት መቻሉን ተናግረዋል።

በቂ ውሃና ለም መሬት የሚገኝበት ቦታ እስካሁን ሳይለማ መቆየቱ የሚያሳዝን ቢሆንም አሁን ላይ በአትክልትና ፍራፍሬ እያስገኘን ያለው ውጤት ግን ተስፋ ሰጪ ነው ብለዋል።

## "ያለ ህዝብ ንቁ ተሳትፎ ከተማና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ድምጻዊት ፀደኒያ ገብረማርቆስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፀችው፤ ህዝብ በአገር ልማት ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆን አለበት እንጂ ሀገርን የሚያስተዳድረው መንግሥት ከሚሰጠው በረከት ብቻ ቁጭ ብሎ ለመቋደስ መጠበቅ አይገባውም።

በልማቱም ሆነ ሰላም በማረጋገጡ መንግሥት እየተወጣ የሚገኘው የህዝብን ኃላፊነት ጭምር መሆኑን የጠቆመችው ድምጻዊት ፀደኒያ፤ ህዝቡ በልማትም ሆነ የአካባቢውን ሰላም በማስጠበቅ ረገድ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የመንግሥትን ጫና ሊጋራ እንደሚገባውም አመልክታለች።

እንደ ድምፃዊት ፀደኒያ ገለጻ፤ ህዝብን እንደ ህዝብነቱ የኔነት ስሜት ተሰምቶት በሁሉም የልማት ሥራዎች ተሳትፎ ማድረግ ይኖርበታል።ይህ ሲሆን ተጠቃሚነቱም እየጨመረ ይመጣል፡፡

ግለሰቦች አቅም ኖሯቸው ሀገርን ለመገንባትና ለማልማት ከሀገር ሀገር ሲመላለሱ መንግሥትም በበኩሉ ግለሰቦች በሀገሪቱ በየትኛውም ጫፍ ላይ ለመስራት የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታና ስርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባው ድምጻዊት ፀደኒያ ገብረማርቆስ ገልጻለች።

ድምፃዊት ፀደኒያ መንግሥት ግለሰቦች በሰላም ወጥተው የሚገቡበት ሰላማዊ ሀገርን መፍጠር እንደሚገባው አመልክታ፤ መንግሥት የህዝብን ሰላም በማስፈንና መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ እንደሚገባውም ጠቁማለች።

ህብረተሰቡም መንግሥት ለሚያከናውነው ተግባር አጋዥና ሀገርን ለማሳደግ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ሊወጣ እንደሚገባው የገለፀችው ድምጻዊት ፀደኒያ፤ መንግሥት ህዝብ ሰርቶ የሚያድርበት ነግዶ የሚያተርፍበትን ሰላም የማስጠበቅ ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባውም ተናግራለች።

መንግሥት እንደ ሀገር አስተዳዳሪነቱ ከተማና ሀገር የማልማት ሥራ መስራት ብቻ ሳይሆን የህዝብን ሰላም የማስፈን ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣም ድምጻዊት ፀደኒያ ገብረማርቆስ ጥሪዋን አቅርባለች።

ጥቅማቸው የተነካባቸው ግለሰቦች ሀገርን ለማፍረስ ሊሰሩ ይችላሉ ያለችው ድምፃዊት ፀደኒያ ገብረማርቆስ ፤በአንጻሩ ጥቅማቸውን ትተው ለሀገራቸው የቆሙ ሰዎች ግን ሀገርን ያስቀጥላሉ።ለእነዚህን ሰዎች ሁለተናዊ ድጋፍ በማድረግና ለሀገር ቅድሚያ በመስጠት ሀገርን ማሻገር ይገባልም ብላለች።

እያንዳንዱ የሀገሪቱ ዜጋም በግለሰብ ደረጃ አዲስ አበባ ከተማ ላይ ብቻ ተወስኖ ሳይቀር በሁሉም የኢትዮጵያ ጥግ ድረስ በመሄድ የማልማት ሥራ መከወን ይገባል ያለችው ድምጻዊት ፀደኒያ፤ መንግሥትም በበኩሉ የዜጎቹን መሰረታዊ ፍላጎቶችና የመሰረተ ልማቶች ማሟላት አለበት ስትል ገልጻለች።

## የአማራ ባንክ ሁሉንም በእኩልነት በማገልገል...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የአክሲዮን ሽያጭ 185 ሺህ ባለ አክሲዮኖችን ማፍራቱን አውስተው፤በዚህም በስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር የተፈረመና አምስት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር የተከፈለ ካፒታል መሰብሰቡን ጠቁመዋል።

የባንኩን ሥራ መጀመር ምክንያት በማድረግም በትናንትናው ዕለት ለሚወለዱ ህጻናት በባንኩ የ2000 ብር ሂሳብ እንደሚከፈትላቸው እንዲሁም በአዲስ አበባ የአንበሳ አውቶብስ ተጠቃሚዎች በነጻ እንዲጠቀሙ ባንኩ ሙሉ ወጪውን መሸፈኑን ተናግረዋል።

በመላ አገሪቱ የሚገኙ 72 ሙሉ የባንክ አገልግሎት የሚሰጡ የባንኩ ቅርንጫፎችም በይፋ ሥራ የጀመሩ ሲሆን የባንኩን ሥራ መጀመር በጉጉት ሲጠባበቁ የነበሩ በርካታ ደንበኞችም በዕለቱ በደንበኝነት ተመዝግበዋል።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ በበኩላቸው መንግሥት መልካም ፖሊሲ ቀርፆ ድህነትን ለማስወገድ ከፍተኛ ርብርብ እያደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ አማራ ባንክ በርካታ ሀሳቦችን አዋህዶ አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን አቀናጅቶ በአገሪቷ የባንክ ኢንዱስትሪ በካፒታል መጠኑ እና በባለአክሲዮኖች ብዛት የመጀመሪያ የሆነውን ባንክ አደራጅቶ ለዚህ በመብቃቱ እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል።

የብሔራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ ባንኩ በገጠር እና በከተማ ከፍተኛ የአክሲዮን ሽያጭ ያከናወነ እና በአገሪቱ በርካታ ባለአክሲዮኖች ያሉት ባንክ መሆኑን አመልክተው፤ የባንኩን የቦርድ አመራሮች እና አባላትን አመስግነዋል።

በአንድ ቀን 72 የባንክ ቅርንጫፎችን መክፈት ከባድ መሆኑን ጠቁመው፤ ባንኩ በዚሁ ከቀጠለ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትልቅ እና ተወዳዳሪ እንደሚሆን እምነታቸውን ገልጸዋል።

ብሔራዊ ባንክም ለሌሎች ባንኮች እንደሚያደርገው ሁሉ ለአማራ ባንክ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

በምርቃት ሥነ ሥርዓቱ ላይም ፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባዔ አቶ አገኘሁ ተሻገር፣ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ፣የብሔራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴና ሌሎች የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የባንኩ የቦርድ አመራሮች እና ሌሎች እንግዶች ተገኝተዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ዘመን የተሻገረው የምርመራ ጋዜጠኝነት

በሀገራችን መልክዓ ሀሰተኛ መረጃ ፣ ሚርት ፣ ትርክትና የሴራ ፖለቲካ ገዥ ሆነው የወጡት ብዙኃን መገናኛዎች ከሁነት ፣ ከስብሰባና ከፕሮቶኮል ዘገባ አዙሪት ወጥተው የምርመራ ዘገባ ባለመስራታቸውና በሀገሪቱ ሳሎን ነጫጭ ዝሆን የሆኑ ጉዳዮችን ባልሰማና ባላየ ማለፍን በመምረጣቸው ነው ። ሰሞኑ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር በፓርላማ ቀርበው ካነሷቸው ሶስቱን በአብነት እንመልከት ። "ሌብነት ፣ ተረኝነትንና ፋኖ"፤ በሀገሪቱ ስለተንሰራፋው ሙስናና አይን ያወጣ ሌብነት ሚዲያዎቻችን ቀድመው አጀንዳ አድርገው ንቅናቄ ሊፈጥሩበት በተገባ ነበር ። ሌላው በሀገሪቱ ተረኝነት ሰፍኗል የሚለው አደገኛ የተዘባ መረጃ ለውጡ ከባተ ጀምሮ የነበረ ነው። ይሄን የተዛባ መረጃ በተለይ የመንግሥት ብዙኃን መገናኛዎች በምርመራ ጋዜጠኝነት መንገድ ሄደው በእርግጥ ተረኝነት አለ ወይስ የለም የሚለውን መርምረውና አጣርተው አበክረው ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ይገባቸው ነበር።

በአማራ ክልል እየተካሔደ ባለው የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ እንቅስቃሴ ፋኖ እየተሳደደ እየታሰረ ነው፤ መንግሥት ትጥቅ ሊያስፈታው ነው የሚለውን በሴራ ፖለቲካ የተዳወረ ሀሰተኛና የተዛባ መረጃን ሚዲያው ደርሶ አጣርቶና መርምሮ ይፋ ሊያደርገው ሲገባ አለማድረጉ በተወሰነ ደረጃ ውዥንብርና ግርታ መፍጠሩ አልቀረም ። ስለ ተረኝነትም ሆነ ፋኖ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ እስኪሰጡ መጠበቅ አልነበረበትም። አሁንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የገለጹትን መሬት ላይ ወርዶ በማመሳከርና በማረጋገጥ ወይም ተከታይ ዘገባ/follow up/በማጠናቀር ሀሜታውን መቋጨት ያሻል ። ሚዲያው ከአጀንዳ ተቀባይነት አባዜ ወጥቶ አጀንዳ ቀራጭና የሕዝብ አስተያየት መሪ ወደ መሆን ሊሸጋገር ይገባል።

በርካታ ምርመራና ማጣራት የሚሹ ጉዳዮች በራሱ ተነሳሽነት ከስር ከስርና ወዲያው ወዲያው እያጠናቀረ ሕዝብን ከበሬ ወለደና ከሀሰተኛ መረጃ መታደግ አለበት። ጉዳዩ ፓርላማ እስኪደርስና ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ እስኪሰጡበት መጠበቅ የለበትም። ይሂን ለማድረግ ደግሞ በተለይ ኢቲቪ ፣ ኢዜአና ፕሬስ ኤጀንሲ የምርመራ ጋዜጠኝነት ቡድን ካላቋቋሙ ሌላው ቢቀር በማሕበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ዘርፍ ሊያቋቁሙ ይገባል። እያንዳንዱ ዘርፍ ደግሞ ተመራማሪዎችና አማካሪዎች ሊኖሩት ይገባል ። ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው ነውና ኢትበሀሉ የመንግሥት ብዙኃን መገናኛዎች ከተለመደ አሰራር ወጥተው ፤ ከመንሸራተት ተጠንቅቀው ፤ አዲሱን ወይን በአዲሱ አቁማዳ ማጋባት ይጠበቅባቸዋል። ለመንደርደሪያነት ይሄን ካልሁ ወደ ተነሳሁበት ርዕሰ ጉዳይ ልመለስ።

የምርመራ ጋዜጠኝነት ሲወሳ እሱ በዚያ አለ ። የምርመራ ጋዜጠኝነት አውራ ምሳሌ ነው። ወዲህ ዳናውም ጥላውም ነው። ወዲያ የምርመራ ጋዜጠኝነትን ያለ እሱ ማሰብ አይቻልም። ዘውድና ጎፈር ነው። አንድም ሁለትም። እንደፈንጅ ጠራጊ አይለያዩም። የምርመራ ጋዜጠኝነት መደምደሚያና ጉልላትም ነው ። "ዋሽንግተን ፖስት"ን ከምንም አንስቶ በጋዜጠኝነት ዙፋን በግርማ የኮፈሰ ባለውለታው ነው። የ "ዋሽንግተን ፖስት" የምርመራ ጋዜጠኞች ቦብ ውድዋርድና ካርል በርንስቴን ስም ያሰሩት ፤ እውቅና ያገኙት ፤ ዝናቸው ከአጽናፍ አጽናፍ የናኘው ፤ የጻፉት አይደለም አርትኦት የሰሩለት መጽሐፍ እንደ ከረሚላ በመላው ዓለም የሚቸበቸበው የማያረጀውን "የዋተርጌቴ" ቅሌት በሕይወታቸው ተወራርደው በማጋለጣቸውና በሥልጣን መባለግን አነውረው ፤ የሕግ የበላይነትን በማይናወጥ አለት ላይ በመመስረታቸው ነው ። እንደ ሰሞነኛው የአማራ ባንክ ማስታወቂያ በየደጁ ሲያንኳኳ "ከጎንህ ማነው!?" ተብሎ ሲጠየቅ መልስ ሳይሰጥ ከርሞ ሰሞኑን ይፋ እንደሆነው ፤ ከፍ ብዬ በተለያየ መንገድ ልገልጸው የሞከርሁት ያው "ዋተርጌት"ን መሆኑን ደርሳችሁበታል ። ትላንት አርብ ሰኔ 9 ቀን 2014 ዓ.ም 50 ዓመት ሞልቶት እንኳ ሰርክ አዲስ ነው። የያዝነውን ዓመት ጨምሮ ባለፉት ዓመታት ከ20 በላይ ፊልሞች ተሰርተውለታል ። በርካታ መጽሐፍትና ዶክመንተሪዎችም ተሰናድተውለታል ።

ታሪኩ እንዲህ ነው ፤ የፕሬዝዳንት ኒክሰን አስተዳደር የላካቸው አምስት ሰርሳሪዎች በወርሀ ሰኔ 17 ቀን 1972 ዓ፣ም በዋሽንግተን ዲሲ ዋተርጌት ሕንጻ ላይ የሚገኘውን የዴሞክራቶችን ዋና መስሪያ ቤት ጨለማን ተገን አድርገው ሰብረው በመግባት ከምርጫ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ከመስረቅ ባሻገር ሚስጥራዊ የድምጽ መቅረጫና ካሜራ አስቀምጠው ይወጣሉ። ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ሲውሉ የተገኘባቸው ረብጣ ዶላር ምንጭ በአቃቤ ሕግና በመርማሪ ጋዜጦች ሲጣራ በቀጥታ ፕሬዝዳንት ኒክሰንን ለ2ኛ ጊዜ ለማስመረጥ ከተሰየመው የምርጫ ኮሚቴ ጋር ይገናኛል። የኒክሰን አስተዳደር ራሱን ከዚህ ወንጀል ነጻ ለማውጣት ያደረገው መላላጥ ነው እንግዲህ የዋተርጌት ቅሌት የተባለው ።

የሰርሳሪዎች ጉዳይ ከሪፐብሊካኖች የምርጫ ኮሚቴ ጋር መያያዙና የአዳዲስ መረጃዎች ይፋ መሆንን ተከትሎ የአሜሪካ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለተጨማሪ ምርመራ ለሕግ አውጭ ኮሚቴ መራው። የሕግ መወሰኛ ምክር ቤትም(ሰኔቱ)በፊናው የዋትርጌት ኮሚቴ በማዋቀር ማጣራቱን ተያያዘው ። ሒደቱ በጋዜጦች ፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሰፊ ሽፋን ያገኝ ስለነበር ያለልዩነት የአሜሪካውያንን ቀልብና ትኩረት ሳበ ። በተለይ በሴኔቱ ጉዳዩ መታየትና መሰማት (hearing) እንደጀመረ በPBS ሽፋን ማግኘቱ አሜሪካውያን ምርመራውን በጉጉት በጥፍራቸው ቆመው ይከታተሉት ጀመር ። ፕሬዝዳንት ኒክሰን ወንጀሉን ለማለባበስና ለመሸፋፈን አማካሪዎቻቸው ያቀረቡላቸውን ዕቅድ ያለምንም ማቅማማት አጽድቀው አፈጻጸሙን በቅርብ ይከታተሉ እንደነበር ምስክሮች ለሴኔቱ ካጋለጡ በኋላ ጉዳዩ ከፓርቲ ፖለቲካነት አልፎ የሕዝብና የሀገር ጉዳይ ሆነ ። የኒክሰን አስተዳደር ምርመራውን ለማስተጓጎል የተለያዩ ጋሬጣዎችን በመጋረጥና ለምርመራው ለመተባበር እግሩን ይጎትት ስለነበር ሕገ መንግሥታዊ ቀውስ ለመፍጠሩ ተቃርቦ ነበር።

ትላልቅና አስደንጋጭ መረጃዎች መውጣት ሲጀምሩ የኒክሰን አስተዳደርም በዛው ልክ ምርመራውን ለማደናቀፍ በስፋት እየተንቀሳቀሰ መሆኑ ሲደረስበት በፕሬዝዳንቱ ላይ ክስ ወይም impeachment ተመሰረተ። ይሄን ተከትሎ የሀገሪቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በነጩ ቤተ መንግሥት የሚገኙ ሚስጥራዊ የድምጽ ቅጂዎችን የያዙ ካሴቶች ለመንግሥት መርማሪዎች ተላልፈው እንዲሰጡ ወሰነ ። ቅጂዎቹ ሲደመጡ ፕሬዝዳንቱ ምርመራውን ለማደናቀፍ ማሻጠራቸውንና የምርመራ ሒደቱን አቅጣጫ ለማስቀየርም የሚመለከታቸውን የፌዴራል ባለሥልጣናትን ለመጠቀም መሞከራቸውን አጋለጡ ። የሕግ አውጭ ኮሚቴው ፕሬዝዳንት ኒክሰን ሶስት አንቀጾችን በመተላለፍ እንዲከሰሱ ወሰነ ። የፍርድ ሒደትን በማደናቀፍ ፤ ሥልጣንን አላግባብ በመጠቀምና ለምክር ቤቱ ባለመታዘዝ በሚል ። ይሄን ተከትሎ ወንጀሉን ለመደበቅ ተባባሪ መሆናቸው ተረጋገጠ ።

ወዲያው ደጋፊዎቻቸውና ፓርቲያቸው አይንህን ለአፈር አሏቸው ። ፕሬዝዳንቱ በነሐሴ 7 ቀን 1974 ዓ.ም ሥልጣናቸውን በገዛ ፈቃዳቸው ለቀቁ ። ይህን ባያደርጉ ኑሮ ክሱ ቀጥሎ በሰኔቱ ውሳኔ ከሥልጣናቸው ይባረሩ ነበር ። ሥልጣኑን በገዛ ፈቃዱ የለቀቀ የመጀመሪያና ብቸኛ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ሆኑ ። በእግራቸው የተኳቸው ምክትል ፕሬዝዳንት ጄራልድ ፎርድ ወዲያው ምህረት አደረጉላቸው ። በዚህ ቅሌት 69 የፕሬዝዳንት ኒክሰን ተባባሪዎች የተከሰሱ ሲሆን በ48 ዋና ዋና የአስተዳደሩ አመራሮች ላይ የተለያየ ቅጣት ተላለፈ ። የፍርድ ሒደቱ የኒክሰን አስተዳደር በሚስጥር የተቀናቃኝ ፓርቲንና የተፎካካሪ ፖለቲከኞችን ቢሮዎች መሰርሰሩን ፤ ሲአይኤን ፣ ኤፍቢአይንና የሀገር ውስጥ ገቢ መስሪያቤትን ፖለቲካዊ መጠቀሚያ ማድረጉ ተደረሰበት ። ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ ከእያንዳንዱ ቅሌት በኋላ gateን በባዕድ መዳረሻነት ወይም ቅጣያነት (suffix_gate) መጠቀም እየተለመደ የመጣው ። ፕሬዝዳንት ኒክሰንን ለ2ኛ ጊዜ ለማስመረጥ የተቋቋመው ኮሚቴ የፋይናንስ አማካሪ ጎርደን ሊዲ ይሄንን ጦሰኛና በዴሞክራት ፓርቲ ላይ ያነጣጠረ አይነት ብዙ ወንጀል የምረጡኝ ዘመቻ የደህንነት ዕቅዱን ለኮሚቴው ምክትል ሊቀመንበር ስቱዋርት ማግሩደር ፤ ለፕሬዝዳንቱ አማካሪ ጆን ዲን ፣ ለጠቅላይ አቃቢ ሕጉ ጆን ሚቼል ያቀርባል ።

የ20ኛው ክፍለ ዘመን ታላቁ ፖለቲካዊ ቀውስና ፕሬዝዳንት ኒክሰን ሥልጣን እንዲለቁ ያስገደደው ቅሌት የሚጀምረው ከዚህ ዕቅድ ነው ይላል ጆን ዲን በቁጭት። የሕግ ቃፊርና መከታ ይሆናል ተብሎ ሲጠበቅ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ጆን ሚቼል ዕቅዱን ከጅምሩ ከመቃወም ይልቅ ለአፈጻጸም እንዲያመች ሆኖ እንዲከለስ አስተያየት ሰጠ ። ከሁለት ወራት በኋላ የዴሞክራት ዋና መስሪያቤትን ሰብሮ ሚስጥራዊ ሰነዶችን የመስረቅ እና ከኋይታወስ ጋር የሚያገናኝ የድምጽ መቅረጫና ሰነዶችን ፎቶ እያነሳ የሚልክ መሳሪያ በድብቅ የማስቀመጡን ሴራ አጸደቀ ። የሴራው ሽራቢ ጎርደን ሊዲ ዕቅዱን በበላይነት ማስተባበሩን በህቡዕ ተያያዘው ።

የፕሬዝዳንቱ የምርጫ ኃላፊ ዋልተር ማኮርድ ቀድሞውን የኤፍቢአይ ወኪል አልፍሬድ ባልድዊንን የድምጽ መቅጃውንና የሰነድ ፎቶማንሻ መሳሪያውን በዴሞክራቶች ዋና መስሪያ ቤት በሚስጥር እንዲያጠምድ በመመደብ ዕቅዱን ማስፈጸም ጀመረ ። የምርመራ ጋዜጠኛው ጂም ሆጋን ማኮርድ ባልዳዊንን የመረጠው እንደሱ የደህንነት ሰው ስለነበረ ነው ይላል። ከዴሞክራቶች ዋና ጽህፈት ፊት ለፊት አስፋልት ተሻግሮ በሚገኘው ሀዋርድ ጆንሰን ሞቴል በማኮርድ ኩባንያ ስም ባልድዊን ክፍል ይያዛል ። በዚህ ክፍል ሆነው ትዕዛዝ ይጠባበቁ የነበሩ ግብረ አበሮች ፤ ከሊዲና ከሀንት ትዕዛዝ ሲደርሳቸው ጨለማን ተገን አድርገው የመጀመሪያውን ስርሰራ አካሂደው መሳሪያዎችን ገጥመው ይመለሳሉ ይለናል ጂም።

ይሁንና ይላል አነፍናፊው ጋዜጠኛ ጂም ፤ በዴሞክራቶች የምርጫ ኃላፊ ስፔንሰር ኦሊቨር የግል ስልክ ላይ የተገጠመውን ድምጽ መቅጃ ለማስተካከል ሰርሳሪዎች በበነጋው በውድቅት ሌሊት ወደ ዋተርጌት ይመለሳሉ ። የህንጻው የዕለቱ የጸጥታ ሰራተኛ ፍራንክ ዊሊስ የተለመደ የጥበቃ ስራው ለማካሄድ ቅኝት በማድረግ ላይ ሳለ በየበሮቹ ቁልፍ ማስገቢያዎች ላይ ቀጫጭን ገመዶችን ይመለከታል ። ባጋጣሚ የተገኙ እንጂ ሌላ የተለየ ነገር ያላቸው ስላልመሰለው ያነሳቸውና ወደ ጥበቃ ክፍሉ ይመለሳል ። ዊሊስ እንዳሰበው ገመዶቹ በአጋጣሚ የተገኙ ሳይሆኑ በሮች እንደተዘጉ ግን ደግሞ እንዳይቆለፉ የሚያደርጉ ነበሩ። ከሰዓታት በኋላ ጥበቃው ለተመሳሳይ ቅኝት ሲመለስ ያነሳቸው እነዛው ገመዶች ተመልሰው በየበሮቹ የቁልፍ ማስገቢያ ተንጠልጥለው ይመለከታል። በሁኔታው ይደናገጥና ለፖሊስ ይደውላል።

ባጋጣሚ ስልኩን ያነሱ ፖሊሶች የአደንዛዥ ዕጽ አዘዋዋሪዎችንና የመንገድ ላይ ወንጀለኞችን ለመያዝ የወጡ ስለነበር ማንነታቸው እንዳይታወቅ እንደዘመኑ ወጣቶች ለብሰው ተመሳስለውና መኪናቸውም እንዳትለይ እንዲሁ የሲቪል ነበረች። ከዋተርጌት ሕንጻ ፊት ለፊት በሚገኘው ሀዋርድ ጆንሰን ሆቴል ክፍሉ በረንዳ ሆኖ በዋተርጌት አካባቢ አጠራጣሪ ነገርና ጸጉረ ልውጥ ሰው ከተመለከተ የዴሞክራቶችን ቢሮ ሰብረው ለገቡት ሰርሳሪዎች ማንቂያ መልዕክት እንዲያስተላልፍ የቀድሞው የኤፍቢአይ ወኪል አልፍሬድ ባልድዊይን ተመድቧል ።

ሆኖም የተጣለበትን ኃላፊነት ችላ ብሎ ፊልም እያየ ስለነበር ፖሊሶችንም ሆነ መኪናቸው በዋተርጌት ሕንጻ ፊት ለፊት እየሆነ የነበረውን አላየም ። አልሰማም። ፖሊሶቹ 6ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 29 ላይ እስኪደርሱ አልፍሬድ አይኑን ከዋተርጌት ሕንጻ ይልቅ ፊልሙ ላይ እንደተከለ ነው ። ድንገት ወደ ሕንጻው ሲመለከት 6ኛ ፎቅ ላይ ያልተለመደ እንቅስቃሴ ያስተውላል። ወዲያው ይደናገጥና እየተጣደፈ ሬዲዮውን አንስቶ ለሰርሳሪዎች የማስጠንቀቂያ መልዕክት ለማስተላለፍ ሲሞክር ነገሮች ሁሉ አከትሞላቸዋል ። ፖሊሶች አምስቱንም ሰርሳሪዎች እጅ ከፈንጅ ያዟቸው ። በወርሀ መስከረም አጋማሽ 1972 ዓ.ም አምስቱን ሰርሳሪዎችን ጨምሮ ሀንትና ሊዲ ሴራ በማሴር ፣ ቢሮ ሰርስሮ በመግባትና የፌዴራሉን ስልክ የመጥለፍ ሕግ በመተላለፍ ክስ ተመሠረተባቸው። ለነገሩ ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስስ አይለቅም እንዲሉ ፤ ሀንትና ሊዲ የደህንነት መረጃዎች ማሾለክን ለማስቆምና ጥብቅ ሚስጥራዊ መረጃዎች ለማጣራት በሚል በህቡዕ የተደራጀና "White House Plumbers"በመባል የሚታወቀው ህቡዕ ቡድንም አባል ናቸው ።

ተማምለው የሸረቡት ሴራ ሲጋለጥ መከዳዳት ያለነውና የፕሬዝዳንት ኒክሰን አማካሪ የነበረው ዲን በኋላ ላይ በሰጠው ቃል ፤ የኒክሰን 2ኛ ምርጫ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ጆን ኤህሪሊችማን ከዋተርጌት ጋር የተያያዙ በተለይ የሀዋርድንና የኋይታወስን ግንኙነት የሚመለከቱ ማስረጃዎችን እንዲያስወግድ አዝዞት እንደነበር ሲል ቢያጋልጥም ጆን ግን ውንጀላውን አስተባብሏል ። መቼም ምን ያለበት ዝላይ አይችልም እንዲሉ በወቅቱ ፕሬዝዳንት ኒክሰን በየቀኑ ይሰጡት የነበረ የተምታታ አስተያየት ጥርጣሬ ማጫሩ አለቀረም ። ሆኖም የዋተርጌቱ አቃቤ ሕግ ጀምስ ኒል ፕሬዝዳንት ኒክሰን ስለዴሞክራቶች ቢሮ መሰርሰር የሰሙት ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ ነው ብሎ ያምን ነበር ። ይሁንና በኋላ ላይ የወጡ መረጃዎች ይፋ እንዳደረጉት ፕሬዝዳንቱ የካቢኔ ጉዳዮች ኃላፊ ወይም ቺፍ ኦፍ ስታፋቸው የነበረውን ሀልድማን ኤፍቢአይ ስለዋተርጌት የፋይናንስ ምንጭ የሚያካሂደውን ምርመራ ለሲአይኤ ነገሮ እንዲያስቆመው አዝዘውት ነበር። በወቅቱ ስለጉዳዩ የተጠየቀው የፕሬዝዳንቱ የፕሬስ ኃላፊ ሀልድማን እንደታዘዘው ቢያደርግ ኖሮ ሌላ ቅሌት ይወጣው ነበር ሲል ተሳልቋል ። ሴኔቱም እንዲከሰሱ መወሰኑ እንደማይቀር ፤ ሕዝቡም ጀርባውን እንደሰጣቸው ሲረዱ የነጩ ቤተመንግሥት ቆይታቸው እህል ውሃ እንዳለቀ ተረዱ ።

ፕሬዝዳንት ኒክሰን አስተዳደራቸውንም ሆነ ራሳቸውን ለማዳን ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም ። በገዛ ፈቃዳቸው የማይለቁ ከሆነ በሴኔቱ የተከሳሽ ሳጥን ቆመው፤ ጥፋተኝነታቸው ተረጋግጦና ቅጣት ተላልፎባቸው ፤ ውርደትን ተከናንበው ከሚባረሩ በገዛ ፈቃዳቸው ለቀው ጥቅማ ጥቅማቸውንና የተረፈች ስም ለዛውም እንጥፍጣፊ ካለች ለማዳን ሲሉ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው በወርሀ ነሐሴ 1974 ዓ.ም መራር ውሳኔን ተጎነጩ ። በገዛ ፈቃዱ ሥልጣኑን የለቀቀ የመጀመሪያ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ሆኑ ። አራተኛው መንግሥት ሚዲያ ለሕግ የበላይነት ሸንጡን ገትሮ ተሟግቶ ግዳይ ጣለ። ታሪክ ሰራ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !

አሜን።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# በቶሎ የጠለቀችው የጋዜጠኝነት ጀምበር

እፀገነት አክሊሉ

ከቀኝ አዝማች ወንድማገኝ አለሙና ከወይዘሮ አበራሽ ደስታ በአዲስ አበባ ከተማ፣ ሰንጋ ተራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው የዛሬ 66 ዓመት ገደማ የተወለደችው:: ለአባትና ለእናቷ ሶስተኛ ልጅ ስትሆን አባቷ ሌላ ትዳር መስርተው ያፈሯቸው ስድስት እህትና ወንድሞች አንዳሏት ትናገራለች:: የዛሬ የሕይወት ገጽታ እንግዳችን አንጋፋዋ ጋዜጠኛ ብዙ ወንድማገኝ። (በነገራችን ላይ፣ "ጋዜጠኛ አንቱ አይባልም" ያለችኝን በመቀበል "አንቺ" እያልኩ የምቀጥል መሆኔን ከወዲሁ ማሳወቁ ተገቢ ነው።)

ብዙ ወንድማገኝ አዲስ አበባ ከተማ ተወልዳ ያደገች ብትሆንም ትምህቷን "ሀ" ብላ የጀመረችው ግን ጎላ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ውስጥ በቄስ ትምህርት ቤት ነበር:: ካዛ በፊት ደግሞ በአካባቢያቸው የሚኖሩት የኔታ ወልደጊዮርጊስ ልጆች እየሰበሰቡ ፊደል ያስቆጥሩ ስለነበር ብዙም በእሳቸው ፊደል የመቁጠር እድልን አግኝታለች::

ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ለመግባት ስታስብ ግን ሁኔታዎች ቀላል አልሆኑላትም:: ችግሩ ደግሞ አባትዋ "ሴት ልጅ የጸሎት መጽሐፍ ለማንበብ ፊደል መቁጠርና ዳዊት መድገም በቂዋ ነው" በማለታቸው ነበር::

ብዙ "... አባቴ ሴት ልጅ ዳዊት ከደገመች በቂዋ ነው ስለሚሉ ዘመናዊ ትምህርትን አይደግፉም ነበር:: በእርግጥ ይህ ሁኔታ የአባቴ ብቻ ሳይሆን በዘመኑ የነበሩ አባቶችና እናቶችም ሃሳብ ነበር" ትላለች::

ነገር ግን ተምሮ ትልቅ ቦታ የመድረስ ህልም የሰነቀችው ብዙ በዚህ አባባል ልትሸነፍ ወይንም ደግሞ እንደ አባቷ ሃሳብ ትምህርቱን እርግፍ አድርጋ በመተው ወደ ቤት ስራው ልታመዝንላቸው አልቻለችም:: እንደውም ለእሳቸው እልህ ብላ ሳይሆን አይቀርም ዳዊትን ብቻ ዘጠኝ ጊዜ ከልሳ ስለመማሯ ትናገራለች"

ብዙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን ለመከታተልም ከፍተኛ የሆነ ችግር ገጥሟት ነበር። እንደውም ትምህርት መማሯን የሚደግፍ አንድ ሰው እንኳን ማግኘት ተስኗት እንደ ነበር ታስታውሳለች::

"....ዳዊት መድገም በቂሽ ነው ያሉኝ አባቴ የቤት ስራው ላይ እንዳተኩር ከማድረጋቸውም በተጨማሪ ባል አመጥተው ሊድሩልኝ ማሰባቸውንም ሰማሁ:: ይህ ደግሞ ለእኔ ትልቅ መርዶ ሆነብኝ። እንደውም የታጨልኝ ባልም ቤት ድረስ ይመጣም ነበር" ትላለች ሁኔታውን ስታስታውስ።

ነገር ግን የትምህርትን ጥቅም የሚያውቅ፣ ራሱም የተማረ፣ "ሴትን ልጅ አስተምሮ ክፍ ያለ ደረጃ ማድረስ ነው እንጂ በልጅነት መዳር ጎጂ ልማድ ነው" ብሎ የሚያምን ሰው ከመካከላቸው ተገኘ። እሱም የብዙ ታላቅ ወንድም አማረ ወንድማገኝ ነበር።

አቶ አማረ የብዙ በልጅነት ለትዳር መሰጠት በከፍተኛ ሁኔታ ከመቃወሙም በላይ ከአባቱ ጋር ከፍተኛ የሆነ ጸብ ውስጥ ገባ ፤ አባትም አንተ የልጅቷን ሕይወት ልታበላሽ ነው ትማር የምትለው ሴተኛ አዳሪ ልታደርጋት ነው ፤ በማለት ትልቅ ጸብ ፈጠሩ ትላለች ብዙ፤ በዚህ መካከልም የትምህር ሃሳብ እንዲቆም ቤት እንድውል ተወሰነብኝ በማለት ሁኔታውን ታስታውሳለች።

አቶ አማረ ግን ወትሮውንም ቢሆን የትምህርት ጥቅሙ የገባቸው ነበሩና ስለተማረች አትባልገም፤ በልጅነቷም ትዳርም ስለያዘች እናንተ እንደምታስቡት ስኬታማ አትሆንም ፤ ስለዚህ በእኔ ሃላፊነት ዘመናዊ ትምህርት ቤት ትገባለች ብለው በውሳኔያቸው ጸኑ፤ በዚህም ውሳኔያቸው መሰረት ብዙ ዘመናዊ ትምህርትን ልታገኝ ወደ በየነመርድ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገባች::

ትምህርት ቤት መግባቱ አንድ እርምጃ ሆኖ ሳለ ለትምህርት ቤት ክፍያና ለደንብ ልብስ ገንዘብ እንዲሁም የክፍል ጥበት ስለነበር መቀመጫ ከቤት አምጡ መባሉ ሌላ እንቅፋት ሆነ:: አባትም እነዚህን የተባሉትን ነገሮች ለመሟላት በፍጹም ፍቃደኛ አልሆኑም::

ነገር ግን እንዴ ተወስኗልና አቶ አማረ በወቅቱ ተግባረ እድ ትምህርት ቤት እየተማረ የኪስ ገንዘብ ያገኝ ስለነበር ከገንዘቡ ላይ የደንብ ልብሱን ስምንት ብር አውጥቶ ገዛ የተጠየቀውን መቀመጫ የሚተካ 10 ብር ደግሞ ጎረቤታቸው ኮረኔል ብርሃኑ ሰጧት:: አሁን ሁሉም ነገር ስለተሟላ ጉዞ ወደ ትምህርት ቤት ሆነ::



ፎቶ፡ በፀሐይ ንጉሴ

ጋዜጠኛ ብዙ ወንድማገኝ

"... በዚህ ሁሉ ጉጉት ውስጥ የተገኘው ትምህርት በጣም ደስ ይል ነበር፤ በመሰረቱ እኔ መጀመሪያም ትምህርት ቤት ሳልገባ በተለይም ዳዊት ከደገምኩ በኋላ መሬት ላይ ወድቆ የማገኘውን ጋዜጣ ሁሉ እየለቀምኩ አነብ ነበር፤ ምናልባት ጋዜጠኛ የመሆን ህልሙም የመጣው ከዛ ሊሆን ይችላል፤ " በማለት ስለሁኔታው ታስታውሳለች::

ትምህርቱ ከተጀመረ በኋላም ቢሆን ግን አባቷ ሃሳባቸውን መቀየር አልቻሉም ፤ እሷም እንደ ተማሪ ሆና የሚጠበቅባትን ማሟላት አልቻለችም፤ ጽዳቷን ለመጠበቅ ጊዜ ስለማይኖራት ብሎም የሚከታተል የቤተሰብ አባልም ስለሌለ ሁል ጊዜ ጸጉሯ ቅጫምና ቅማል ይሆናል፤ በዚህ ደግሞ በየሳምንቱ ትምህርት ቤት በሚደረገው ፍተሻ እሷ ትባረራለች:: ነገር ግን ይህም ቢሆን እሷ ለመማር ያላት ጉጉት ቤት እንዳትውል አድርጓታል::

" ... አባቴ እቤት ውዬ ሙያ እንድማር ከዛም ደግሞ ትዳር ይዤ እንድኖር ስለነበር ህልማቸው ቤት ውስጥ የቤት ሰራተኛ እያለ ጠዋት ትምህርት ቤት ከመሄዴ በፊት ተነስቼ ደጅ እንዳፀዳ ውሃ አሙቄ ፊታቸውን እንዳስታጥብ ቁርስ እንዳበላ ወሰኑብኝ:: እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከከወንኩ በኋላ ነበር ትምህርት ቤት የምሄደው" በማለት ለትምህርት የከፈለችውን መስዋዕትነት ታስታውሳለች::

እነዚህን ተግባራት አከናውና ወጥታ ትምህርት ቤት ስትደር ከፍተኛ የሆነ ድካም ከመሰማቱም በላይ ሁል ጊዜ ልብሷ ሊጥ ነክቶት እጆቿ በጥላሸት ተለውሰው ነበር የምትደርሰው፤ በዚህም በትምህርት ቤት ጓደኞቿ ፊት ከመሸማቀቋም በላይ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ደጅ እየጠበቋት ክፍል ከመግባቷ እንድትታጠብ ይነግሯት እንደነበር ታስታውሳለች::

ብዙ ጊዜ ነገሮች አልጋ በአልጋ አይሆኑም ብዙ የገጠማት ነገርም እንደዛው ነው፤ በትግልና በመስዋዕትነት የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን በብዙ ችግሮች መካከል እያለፈች ብትማርም እድል ከእሷ ጋር አልነበረችምና የስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን ማለፍ ሳትችል ቀረች:: ይህ ሁኔታ እሷ ከነበራት የትምህርት ተሳትፎ በቤተሰቦቿ ከማይደረግላት ድጋፍ አንጻር የምትጠብቀው ቢሆንም ነገሩ ግን እጅግ አሳዘናት:: አባቷ ደግሞ ይኸው ያልኩት ይህንን ነው አርፈሽ ተቀመጪ ማለታቸውን ታስታውሳለች::

".... እኔ ትምህርት እማራለሁ ብዬ የገባሁበት አስቸጋሪ ሁኔታ የማልፈው ውጣ ውረድ እውነት ከቤተሰብ ጋር ነው እምኖረው ብዬ ሁሉ እራሴን እንድጠይቅ ያስገደደኝም ነበር፤ በነገራችን ላይ አንድ ጊዜ ትምህርቴ ላይ ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ ሲያሰሙ በቃ ካልተማርኩ ባልም አላገባም ራሴን ባጠፋ ይሻለኛል ብዬ ለመታነቅ ሞክሬ ነበር:: ምን ዋጋ አለው እንደዚህ የለፋሁበት ትምህርት እድል ከእኔ ጋር ባለመሆኑ ስምንተኛ ክፍል ወደቅኩ" በማለት አሳዛኙን የትምህርት ጊዜዋን ትናገራለች::

ነገር ግን ያ ታላቅ ወንድሟ አቶ አማረ በወቅቱ ከተግባረ እድ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት ተመርቆ አሰብ መድሃኒት ማጣሪያ ላይ ስራ ጀምሮ ነበርና፤ ነገሩን ሲሰማ በጣም አዝኖ ብትወድቂም ትምህርትሽ አይቆምም ማለቱ የጠለቀች የምትመስለው የብዙ ፀሀይ በመጠኑም ቢሆን ፈካ አደረገችው:: አቶ አማረ አዲስ አበባ በሚገኘው ጓደኛው አማካይነት ገንዘብ ልኮ የግል ትምህርት ቤት እንድትገባና ከስምንተኛ ክፍል ትምህርቷን እንድትቀጥል አደረገ:: በጉርምስና እድሜ ክልል ላይ የምትገኘው ብዙም ከትምህርት ወጪዋ ባሻገር ሌሎች ወጪዎችም ይኖሩባት ይሆናል በማለትም ገንዘብ መላኩ ቀጠለ::

በዚህ ገንዘብ ደግሞ ጫማ ልብስ እንዲሁም ቅባትና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮቿን እያሟላች ለትምህርት ቤት በወር 25 ብር እየተከፈለላት መማርን ቀጠለች::

"...የስምንተኛ ክፍል ትምህርቴን በወቅቱ በአባሃና ጂማ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት የአሁኑ ጆን ኤፍ ኬኔዲ ትምህርት ቤት በሚባለው በወር 25 ብር እየተከፈለልኝ መማሬን ጀመርኩ:: የመማር ፍላጎት የነበረኝ በመሆኑም ወድቄያለሁ ብዬ አንገቴን ሳልደፋ ትምህርቴን በአግባቡ መከታተል ቀጠልኩ:: በዛው ስምንተኛን ክፍል አልፌ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴንም እዛው ቀጠልኩ" ትላለች::

አሁን አባቷም ተሸነፉ እሷም ራሷን የምታውቅ ኮረዳ ሆነች ስለዚህ እነዛ የምትሰቃይበት ሁኔታ ቀነስ ማለት ጀመረ፤ ወንድሟ ደግሞ ለእሷ ትምህርት የሚከፍለውን መስዋዕትነት በመረዳት መጠንከርን ምርጫዋ አድርጋለች። ብዙ አንድ ጊዜ ነፍሷ ወደጋዜጠኝነቱ አዘንብላለችና ያገኘችውን እድል ሁሉ ትጠቀም ነበር:: የሚሰማት ስታገኝም ስለ ጋዜጠኝነት እንደማውራት የሚያስደስታት ነገር አልነበረም:: አሁን አባሃና ጅማ ትምህርት ቤት ደግሞ ይህንን የሕይወት ጥሪዋን ለማስተናገድ ምቹ ሁኔታ ተፈጠረላት:: ጠዋት ጠዋት ከጸሎት በኋላ የትምህርት ቤቱን ሚኒ ሚዲያ በመጠቀም የተለያዩ ነገሮችን ማቅረብ ጀመረች፤ አድማጭ ማግኘቷ ደስ አሰኛት::

"... በትምህርት ቤት አካባቢ ሰዎች ምን ይሉናል በማለት በሳምንት አንድ ጊዜ ከጸሎት በኋላ መድረክ ላይ እየወጣሁ የተለያዩ ነገሮችን ለተማሪዎች ማቅረብ ጀመርኩ:: የአባ ሃና ጅማን ተማሪዎች በአካባቢው ያሉ ሰዎች የሚሉንን ነገር እየሰበሰብኩ ማስደመጥም ቀጠልኩ:: በዚህም ትልቅ ተቀባይነት አገኘሁ ደስም አለኝ" በማለት ወደጋዜጠኝነቱ ለመቅረብ ያደረገችውን ጥረት ታስታውሳለች::

በዚህ መካከልም የህይወት ጥሪዋ የሆነውን ጋዜጠኝነት ለመቀላቀል የተለያዩ መንገዶችን ማማተሯ አልቀረም፤ ያገኘቻቸውን ትልልቅ ሰዎችም ጋዜጠኛ መሆን እፈልጋለሁ ምን ማድረግ አለብኝ? ወይም ጋዜጠኛ ለመሆን ምን ያስፈልጋል? እያለች ማማከርም አላቆመችም:: ምናልባትም ገንዘብ ያስፈልግ ይሆን በማለትም ለወንድሟ በመናገር ገንዘብ አስልካም ያዘች።

የት ብሔድ ከህልሜ ልገናኝ እችላለሁ ብላ ስታስብም ቀድሞ ወደጭንቅላቷ የመጣላት በአገር ፍቅር ማሕበር የምትታተመው "የኢትዮጵያ ድምጽ ጋዜጣ" ሆነች። ጋዜጣው ወደሚታተምበት ቦታ በመሄድም ለደብዳቤዎች አምድ ጋዜጠኛ ለመሆን ምን ያስፈልጋል የሚል ደብዳቤና ገንዘብ ይዛ ወደዋና አዘጋጁ ፊት ቀረበች:: የወቅቱ ዋና አዘጋጅ አቶ ከበደ አምቢሳ ጽሁፉን በመስጠት ስንት ብር መክፈል እንዳለባት ጠየቀቻቸው፤ እርሳቸውም "ምንድን ነው የምትከፍይው ምንም የሚከፈል ነገር የለም

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



ይልቁንም ተሰጥኦው ካለሽ ጽሁፎችን እየጻፍሽ አምጪ" በማለት እንደሸኟትም ታስታውሳለች፡፡

የመጀመሪያ ሙከራዋ የሆነውና ጥያቄ አዘል የነበረው "ጋዜጠኛ ለመሆን ምን ያስፈልጋል?" የሚለው ጽሁፍ በዋና አዘጋጁ ተቀባይነት በማግኘቱ በማግስቱ ጋዜጣው ላይ ታተመ፡፡ ይህ ጅማሬ ደግሞ ለብዙ ትልቅ እርምጃዎች መነሻ ሆናት፡፡

"... የጻፍኩት ደብዳቤ ተቀባይነት አግኝቶ በማግስቱ ጋዜጣ ላይ ወጥቶ ሳየው በጣም ነው የተደሰትኩት። እሳቸውም እጅግ ስለተማመኑብኝ በእሳቸው ሃላፊነት በየቀኑ የኢትዮጵያ ድምጽ ጋዜጣ ትምህርት ቤቴ ድረስ ትመጣልኝ ጀመር፡፡ በዚህም ከፍተኛ የሆነ መበረታታት በውስጤ ተፈጠረ" በማለት ወደ ጋዜጠኝነት የገባችበትን መንገድ ትናገራለች፡፡

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ባለበት አቁማ ወደሕይወት ጥሪዋ የገባችው ብዙ የአስረኛ ክፍል ተማሪ እንዳለች በጽሁፍ እየተከፈላት በጊዜያዊ ጸሀፊነት በኢትዮጵያ ድምጽ ጋዜጣ መጻፍ ጀመረች። " ... አይ አንዴ በሩ ከተከፈተ በኋላ እኮ ማን ይቻለኝ በቃ የማልጽፈው ነገር ምንድን ነው፡፡ በሙያው እየጎለመስኩ ስሄድ ደግሞ ታዋቂ ከሆኑት ጋዜጠኞች ጋር በጽሁፍ ፍልሚያን ጀመርኩ" ትላለች።

ከእነ ጋሽ ጳጋዬ ገብረመድህን፣ ተስፋዬ ዳባና ከሌሎች ጋር በመሆንም ከጋዜጠኝነቱ በተጓዳኝ በቲያትሩም ለመሳተፍ እድል አገኘች፡፡ ነገር ግን በእድሜዋ ማነስ ምክንያት በተለይም ጋሽ ጳጋዬ ገብረመድህን ስለተቃወሙ መሳተፍ ሳትችል ቀረች፡፡ ይህ ነገር እጅግ የቆጫት ብዙ እንደ አጋጣሚ ሆኖ እነሱ በሚያዘጋጁት ጋዜጣ ላይ አንድ ጃፓናዊ ሕጻን የሂሳብ ሊቅ ሆነ የሚል ዜና አወጡ፤ ውስጧ በእልህ የተሞላው ብዙም ያንን ዜና በመያዝ ልጆች ከመድረኩ መገለል እንደሌለባቸው የሚገልጽና ሃሳባቸውን እርስ በእርሱ የሚያጣላ አርቲክል ጻፈች። በዚህ ጊዜ ትንሿ ጋዜጠኛ በትልልቆቹ ዘንድ ጥቁር ነጥብ ተያዘባት እንደውም እነሱን ማጥቃት የሚፈልግ ሰው እሷን እየተጠቀማት እንዳለ ሁሉ አሰቡ፤ ጋሽ ጳጋዬ ገብረመድህንም ቢሯቸው ድረስ አስጠርተው ጠየቋት እሷም ያላትን ብሶት ተናገረች እርሳቸውም "አሁን አንቺ ያለሽው በነስንዱ ገብሩ ደረጃ ነው፤ ከዚህ በላይ እንድትሆኚ ያስፈልጋል፤ በዚህ መልኩ ግን አትሂጂ" በማለት ምክር ሰጥተው እንደሸኟት ታስታውሳለች፡፡

ብዙ ለጋዜጠኝነት እንደ ስሟ ብዙ መከራን ከፍላለች ፤ የኢትዮጵያ ድምጽ ጋዜጣ በቋሚ ሰራተኝነት ቢቀጥራትም ጋዜጣዋ ብዙ ርቀት ሳትጓዝ ታጠፈች፤ እሷም ወደ አዲስ ዘመን ጋዜጣ በዝውውር ገባች፡፡

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ "ከማጀት እስከ አደባባይ" በሚል የሴቶች ገጽ አምድን ማዘጋጀት ጀመረች፡፡ ወቅቱ የመንግሥት ለውጥ እየተካሄደበት ነበር የእሷ አለቃ ብርሃኑ ዘሪሁንም እንዲሁም ጳውሎስ ኞኞ ባሉበት የሴቶችን አምድ በቋሚነት እየሰራች ህልሟን መኖር ጀመረች፡፡

ዛሬ ላይ ያለን ጋዜጠኞች የመረጃ ምንጮቻችንን ብቻ ተጠቅመን ይሆናል ዜና የምንሰራው፣ የተለያዩ አርቲክሎችን የምንጽፈው ብዙ ግን እንደዛ አይደለም ስትሰራ የነበረው የኖረችውም አንድ ነገር ሆነ የሚል መረጃ ከደረሳት በቦታው ላይ ሄዳ በአይኗ አይታ ከማረጋገጥ በተጨማሪ እሷን ሊያሳትፍ በሚችል ነገር ላይ ተሳትፋ ሆናውና ኖራው ነበር ስትሰራ የቆየች፡፡ ይህ የስራ ሂደቷ ደግሞ የምትሰራቸው ስራዎች ሰውኛ ባሕርይ እንዲኖራቸው ብሎም የሕብረተሰቡን የልብ ትርታ በሚገባ እንዲመቱ አልፎም የተቸገረው ሰው መፍትሔ እንዲያገኝ መቃናት ያለባቸው ነገሮች በመንግሥትና በሚመለከታቸው አካላት የመታየት እድል እንዲያገኙ ያደረገም ስለመሆኑ የሚያውቋት ሁሉ የሚመሰክሩት ሃቅ ነው፡፡

"... የስራ ሂደቱ ጥሩ ነበር ፤ በምፈልገው መልኩም ሰርቻለሁ ማለት ይቻላል፡፡ ስራዎቼን በስማበለው የምሰራ ሳልሆን በቦታው ሄጄ የተቸገሩትን ሰዎች መስዬ ነው የምሰራው፤ በዚህም ውጤታማ የሆኑ ጊዜያትን አሳልፌያለሁ ብል ማጋነን አይሆንም" በማለት ትናገራለች፡፡

"... በአንድ ወቅት የወቅቱ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ምክትል አዘጋጅ አቶ ጳውሎስ ኞኞ ጠዋት ስራ ስንገባ አንድ ነገር ተናገሩ፤ ንፋስ ስልክ የሚባል ሰፈር ማታ ለመዝናናት በወጡበት ጊዜ በርካታ ሴቶችን በመጠጥ ቤት ማየታቸውን በጣም እያጋነኑ ያወራሉ፤ ይሄንን ስሰማም አይ አቶ ጳውሎስ እርሶ በሚገልጹት ልክ ሴቶች በምሽት ስራ ላይ ተሰማርተዋል ብዬ አላምንም ምናልባት የወቅቱ ፋሽን የነበረው "ቬል ሱሪ፣ ሻፍት ጫማና አፍሮ የጸጉር ቁርጥ ሁሉንም አንድ አይነት አድርጎቦት እንዳይሆን" አልኳቸው ግን በፍጹም ሴቶች ናቸው በማለት ተከራከሩኝ። እንግዲያውስ ይህንን ነገር ማጣራት አለብኝ በማለት ማታውኑ ወደጭፈራ ቤት አመራሁና እዛ ከሚሰሩት ሴቶች መካከል አንዷን ቦታው ላይ ስራ ለመጀመር አስቤ እንደመጣሁ በመንገር ቀረብኳት እሷም አዝናልኝ ባልገባበት እንደሚሻል ምክር ሰጠችኝ አይ ግዴለም ብዬ ሁሉንም ነገር እዛው ሆኜ አየሁ፤ አቶ ጳውሎስ ያሉት ነገር እውነት መሆኑን አረጋግጬ ተመለስኩ፤ ከዛም "አንድ ሌሊት በዳንስ ቤት" በማለት አርቲክል ጻፍኩ" በማለት ለስራዋ የምትሄድበትን ርቀት ትናገራለች፡፡

ነገር ግን አርቲክል አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ሳይወጣ የማስታወቂያ ሚኒስትሩ አቶ ተስፋዬ ገብረእግዚ ስላዩት አገሪቱ የሴተኛ አዳሪዎች መናኸሪያ ሆናለች እያላችሁ ነው በማለት ስለተቆጡ እንዳይታተም ሆነ፤ ከዛም በላይ ጸሃፊዋን ማግኘት እፈልጋለሁ ብለው አናገሯት፤ ነገር ግን እርሷ መታረም ያለበት ነገር መታረም አለበት እንጂ እውነታውን መካድ ችግሩ ስር እንዲሰድ መንገድ መክፈት ነው የሚል እምነት ስለነበራት ጽሁፉ አዲስ ዘመን ላይ እንዳይወጣ ቢደረግም በፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ ላይ እንዲወጣ አስደረገች፡፡

በዚህ ጽሁፍ ደግሞ ብዙዎች ደነገጡ ነገር ግን ብዙ ከስራዋ ወደኋላ አላላችም ቀጥላም ማታ ላይ መንገድ ዳር የሚቆሙት ሴቶች ላይ ትኩረት በማድረግ እነሱን ሆና ጎዳና ቆማ ያየችውን የገጠማትን በሙሉ በመጻፍ በወቅቱ መነን በመባል ለምትታተመው መጽሄት አስረከበች፡፡

ከዚህ በኋላ ነበር እስኪ ኢትዮጵያ ቴሌቭዥን በመሄድ ደግሞ ልስራ በማለት ዝውውር በመጠየቅ የሄደችው፡፡ በጣቢያውም አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ስትሰራ የነበረውን ከማጀት እስከ አደባባይ ይዛ ቀጠለች፡፡ በዚህ ስራዋም መላ ኢትዮጵያን ዞራለች ብዙ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲታወቁ ከማድረግ ባሻገር እንዲታረሙም የበኩሏን ተወጥታለች፡፡

ኋላም ይህ የስራ ትጋቷ አልደከም ባይነቷና በሄደችበት ሁሉ ስኬታማ ብሎም የጣቢያውን ተደማጭነት ከፍ የሚያደርግ ስራዋ ተጓዥ ካሜራችን የሚለውን ፕሮግራም እንድታዘጋጅ በአለቆች ዘንድ አስመረጣት፡፡

"... በጋዜጠኝነት ስራ ከ18 ዓመት በላይ ሰርቻለሁ፡፡ ሰርቻለሁ ስልም ከልብ የሆነ ስራን ነው እንደ ዛሬው ቢሮ ቁጭ ብሎ ስራ የለም፡፡ እንደ ዛሬው መኪናው ካሜራው ተመቻችቶ ጉዞ የለም፡፡ መኪና እንደልብ የለም ካሜራም ማግኘት ችግር ነው ገንዘቡም ትንሽ ነው ነገር ግን የሙያው ፍቅር የመስራቱ ፍላጎት ስለነበረ አንዱን ስራ ጨርሼ ቆይ ቤቴ ሄጄ አርፌ ደግሞ ሌላውን እቀጥላለሁ አልልም በዛው ነበር ወደሌላ የምቀጥለው በጠቅላላው ስራው ደስ የሚል ውጤት የሚታይበት ነበር በዚህም በጣም ደስተኛ ነኝ" በማለት ያሳለፈችውን ጊዜ ትናገራለች፡፡

ከዚህ ከምትወደው ስራ ብሎም አገሯን ከማስተዋወቅ ባህልን ለቀሪው ሕዝብ ከማሳየት የነጠላት የኢህአዴግ መንግሥት ወደሥልጣን መምጣት ነው፡፡ በወቅቱ የመንግሥት ለውጥ ሲደረግ ከተቋሙ ከተባረሩ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ሰራተኞች መካከል አንዷ ሆነች።

በወቅቱ ከአምስት ዓመቱ ብቸኛ ሕጻን ልጇ ጋር ከፍተኛ ችግር ውስጥ ገባች፤ ስራ ማጣት ገንዘብ አጥቶ ለመኖር መቸገር ብቻ ብዙ ነገር ደረሰባት፤ ነገር ግን ፕሮፌሰር አስራት የሚመሩት የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት ብዙን በምትሰራው ስራ ያውቋት ስለነበርም ከነልጇ ስትራብ ማየት አንችልም በማለት በቢሯቸው ውስጥ ስራ እንድታገኝ እንዳደረጓት ትናገራለች፡፡

ነገር ግን እዛ መስራቷ ይበልጥ ለመንግሥት አላስደሰተም እንደውም ክትትል እንዲበዛባት ፕሮፌሰር አስራትንም እንድትሰልልላቸው እስከመጠየቅ የደረሰ ተልዕኮ ሁሉ ይሰጧት ጀመር። ምንም እንኳን ከነልጇ ረሃብ እንዳይገላት ያደረጓትን ሰው አሳልፋ ባትሰጥም። ይህ ሁኔታ ከተማው ላይ ለመኖር እንደማያስችላት ተረዳች፡፡ የተለያዩ መንገዶችን በመፈለግ በእስራኤል አገር እየሩሳሌምን ለመሳለም በሚል ከአገሯ ተሰደደች፡፡

ስደት በእስራኤል ከባድ እንደነበር የምትናገረው ብዙ ከምትወደው ስራ ያለአግባብ መሰናበቷ ልጇን እዚሁ አዲስ አበባ ትታ መሄዷ በጠቅላላው ብዙ የሚያስቸግር ነገር ገጠማት ነገር ግን መቋቋም ደግሞ እድሜ ያረዝማልና ለመቋቋም ወሰነች፤ ተቋቁማም አለፈችው፡፡

"... ወደ እስራኤል ስሄድ ከአየር መንገድ ጀምሮ የሚያውቁኝ ሁሉ በቃ እንቺም ልትሰደጂ ነው እያሉ ነበር፤ ይህ ደግሞ ለእኔ ብሶትን ነበር የሚያሰማኝ በጣምም አዝን ነበር፤ የደረሰብኝ በደል እራሱ ይሰማኛል ከዛ ደግሞ ሌላው ፍርሃቴ በአገር ውስጥ የደረሰብኝና ለስደት ያበቃኝ የመንግሥት እንግልት ተከትሎኝ ሄዶ እዛም መጥፎ ነገር እንዳይገጥመኝ ነበር " ትላለች፡፡

ነገር ግን የእድል ነገር ሆኖ ችግሩ አብሯት አልተጓዘም እስራኤል አገር ሄዳ ለመኖር የነበረው አስቻይ ሁኔታ ከባድ ሆነባት ብዝ ዝቅተኛ የተባለውን ሁሉ ስራ እየሰራች ራሷን ለማቆየት ጣረች፡፡ ከዛም ሁኔታዎች በዛው አልቀጠሉም የተሻለ ነገር አግኝታ ወደካናዳ ለመጓዝ በቃች፡፡

ካናዳም ከሄደች በኋላ ኑሮን ለመኖር የሚያስችል የተለያዩ ስራዎችን ብትሰራም የአገሯ ሁኔታ ግን እጅግ ያሳስባት ነበር፤ ልክ እንደሷ በግፍ ከሚወዱት አገራቸውና ስራቸው ተባረው በባዕድ አገር የሚንከራተቱ ኢትዮጵያውያን ሁኔታም እንቅልፍ ይነሳት ነበር፤ ይህ ነገር ያበቃ ዘንድም ደግሞ ከግንቦት ሰባት ጀምሮ ከተለያዩ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር በገንዘቧም በጉልበቷም በእውቀቷም ደጋፊ በመሆን በአገሪቱ የሥርዓት ለውጥ እንዲመጣ ከፍተኛ ትግልን ማድረጓንም ትናገራለች፡፡

ብዙ ዛሬ ላይ የናፈቀችው ለውጥ ቢመጣም እንደ ቀድሞ ለአገሯ ዘብ መቆም ለሙያዋ ደፋ ቀና ብላ መስራት የምትችልበት ሁኔታ ላይ አይደለችም፡፡ እድሜና ስደት ተደማምረው ዛሬ ላይ አቅመቢስ አድርገዋታል፡፡ በደጋግ ኢትዮጵያውያን ወዳጆቿ ድጋፍ ወደምትወዳት እናት አገሯ መግባት ብትችልም ያለችበት ሁኔታ ግን ከባድ ነው፡፡

በጎ ጓደኞቿ ለጊዜው ታርፍበት ዘንድ በተከራዩላት የእንግዳ ማረፊያ ውስጥ ነው ውላ የምታድረው፡፡ አሁን ላይ አንድ ልጇም አብሯት የለም የራሱን ኑሮ መስርቶ እየኖረ ነው፡፡ ብዙ የአገሯን ሴቶች ከሚደርስባቸው ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ይላቀቁ ዘንድ ብዙ የለፋች በዱር በገደሉ በመንቀሳቀስ በኢትዮጵያን እንቃኛት ዝግጅቷ መላ አገራችንን ቤታችን ቁጭ ብለን እንድናውቅ ያደረገችን የጋዜጠኝነት ሙያ የተማረችው ሳይሆን የተሰጣት ነበረች፡፡ አሁን ከኛ የት ነው ያለሽው የሚል ጥየቃችንን ትፈልጋለች።

# የምስራቅ አፍሪካ ማኅበራዊ መስተጋብር-እምቅ የባህልና ኪነጥበብ ሀብቶች

**ዳግም ከበደ**



የምስራቅ አፍሪካ የጥበባት እና የባህል ፌስቲቫል ላለፉት አምስት ቀናት ሲካሄድ ቆይቶ ዛሬ መቋጫውን ያገኛል። “ጥበባትና ባህል ለቀጠናዊ ትስስር” በሚል መሪ ቃል ከሰኔ 07 እስከ ዛሬ 12 ቀን 2014 ዓ.ም እየተካሄደ ባለው በዚህ ፌስቲቫል የዩጋንዳ፣ የቡሩንዲ፣ የደቡብ ሱዳን፣ የሶማሊያ ሀገራት እና የክልል እና የከተማ አስተዳደር የኪነጥበባትና የባህል ልዑክ ቡድን ታድመውበታል፡፡

በፌስቲቫሉ ማስጀመሪያ መርሃግብር ላይ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ  መድረኩ አፍሪካ ያላትን ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ሀብቶቻችንን ለመላው ለዓለም ያሳየንበት ነው ማለታቸው ይታወሳል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ  የምስራቅ አፍሪካን ለማዋሃድ በሚደረገውን ጥረት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ትልቅ ፋይዳ አለው ተብሎ እንደሚታመን አንስተው ነበር።

ዘመናት የዘለቀውን የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የጋራ ግንኙነትን በጠንካራ መሰረት ላይ ለማስቀጠል ትክክለኛ ወቅት እንደሆነ በማውሳትም  ማንም ብቻውን በመቆም ጠንካራ ሊሆን እንደማይችል ሁሉ፣ ማንም ብቻውን በመሮጥ አሸናፊ ሊሆን እንደማይችል በሚገባ ተረድተን በዓለም አቀፉ የውድድር መድረክ ላይ ሁላችንም ጠንካራ እና አሸናፊዎች እንድንሆን ያሉትን እውነታዎች መረዳት እና አንድነታችንን ማጠናከር ይገባል ሲሉ መልእታቸውን አስተላልፈዋል።

### የምስራቅ ባህላዊና ኪነ ጥበባዊ አፍሪካ ሀብቶች

“የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የተጎናጸፍናቸውን የተፈጥሮ በረከቶች ከባህላዊ እሴቶች ጋር በማጣጣም የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ማጠናከር ያስፈልጋል። ይህንንም እንደ ዋና ዘዴ ከመጠቀም ባሻገር  በዋጋ ሊተመኑ የማይችሉ ንብረቶች ከመላው ዓለም የሚመጡ ጎብኚዎችን በኩራት የሚያዩት ሀብቶች ናቸው” የሚል ጠንካራ አመለካከትን ያነገበው  ይህ ፌስቲቫል አገራቱ የባህል ዲፕሎማሲ ለኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ዲፕሎማሲ እንደ ቅድመ ሁኔታ እንዲቆጠር ሁነኛ መነሻ እንደሆነ ታምኖበታል። የፌስቲቫሉ መካሄድ ምስራቅ አፍሪካን ለአህጉሪቱ እና ለዓለም አቀፍ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የስበት ኃይል ማዕከል ለማድረግ በሚደረገው ረጅም ጉዞ እንደ መነሻ ሊወሰድ እንደሚችልም ተስፋ ተጥሎበታል። ለዚህም በመጪዎቹ ዓመታት ፌስቲቫሉ በእርግጠኝነት ሁሉንም የአህጉሪቱን ሀገራት የማካተት አድማሱን እንደሚሰፋ አዘጋጆቹ ገልጸዋል።

ባለፉት ቀናት  ከምስራቅ አፍሪካ አንዳንድ አገራት ተወክለው በመስቀል አደባባይ፣ አንድነት ፓርክና ልዩ ልዩ የዝግጅት ስፍራዎች ባህላቸውን በተለይ ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣ አለባበስና የአመጋገብ ሥርዓታቸውን ሲያሳዩና ልምድ ሲለዋወጡ ከነበሩት መካከል  የዝግጅት ክፍላችን የመዝጊያ ሥነስርዓቱን ምክንያት በማድረግ ያላቸውን ባህላዊ ሀብቶችና የቱሪዝም እምቅ አቅም ሊያስተዋውቃችሁ ወድዷል። ይህ መረጃም በቀጣይ ጊዜያት ጥምረታቸውና አንድነታቸው እየጎለበተ ለሚመጣው የምስራቅ አፍሪካ አገራት የሚኖረንን ትውውቅ እንደሚያጠናክርልን ተስፋ እናደርጋለን።

### ዩጋንዳ

ዩጋንዳ የምስራቅ አፍሪካ የጥበባት እና የባህል ፌስቲቫል የልኡክ ቡድን ከላኩና ከተሳተፉ አገራት መካከል አንዷ ነች። ከእምቅ የባህልና ኪነ ጥበብ ሀብቶች ባሻገር በኡጋንዳ ያለው ቱሪዝም በመልክዓ ምድር እና በዱር አራዊት ላይ ያተኮረ ነው። በ2012 እስከ 13 የፋይናንስ ዘመን 4 ነጥብ 9 ትሪሊዮን የኡጋንዳ ሽልንግ (1 ነጥብ 88 ቢሊዮን ዶላር ወይም 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዩሮ) ለኡጋንዳ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት በማዋጣት ዋና የስራ፣ የኢንቨስትመንት እና የውጭ ምንዛሪ ያስገኘ ዘርፍ እንደሆነም ይነገራል።

የኡጋንዳ ቱሪዝም ቦርድ የኡጋንዳ ቱሪዝም መረጃን የመጠበቅ ሃላፊነት አለበት። ዋናዎቹ መስህቦች በብሔራዊ ፓርኮች እና በጨዋታ ክምችት በኩል የፎቶ ሳፋሪስ ናቸው። ሌሎች መስህቦች በማጋሂንጋ ጎሪላ ብሄራዊ ፓርክ (ኤምጂኤንፒ) የሚገኙትን የተራራ ጎሪላዎችን ያጠቃልላሉ።

በአፍሪካ ውስጥ እጅግ ጥንታዊ የሆነ የባህል መንግሥት ያላት ዩጋንዳ ብዙ የባህል ስፍራዎች አሏት። ዩጋንዳ ከ1073 በላይ የተመዘገቡ የአእዋፍ ዝርያዎችን የያዘች የወፍ ገነት ስትሆን ከአፍሪካ የወፍ ዝርያዎች 4ኛ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ 16ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ዩጋንዳ ነጭ ካባ ካላቸው የ ሪዎንዜሪ (Rwenzori) ተራሮች እስከ ታላቁ ስምጥ ሸለቆ ድረስ ያሉ መልክአ ምድሮች አሏት።

### ባህል

የኡጋንዳ የረዥም ጊዜ ታሪክ ቢኖርም ሕዝቡ አሁንም ብዙ ልዩ ባህሎቻቸውን ይዘው መቆየት ችለዋል። የባንቱ ተናጋሪዎች በአብዛኛው የሀገሪቱ ባህል ላይ ተጽዕኖ አሳድረዋል። በሰሜን ላንጎ እና አቾሊ ጎሳዎች ጎልተው የሚታዩ ሲሆን በምስራቅ የኢቴሶ እና የካራሞጆንግ ጎሳዎች ይታያሉ። በምእራብ ዩጋንዳ የሚገኙት የዝናብ ደኖች አሁንም በፒግሚዎች ይኖራሉ። የቡጋንዳ ህዝብ ከኡጋንዳ ጋር ያስተዋወቀው ባህላዊ ካንዙ አሁንም የወንዶች ብሄራዊ አለባበስ ሲሆን ሴቶቹ በጎሜሲ ለብሰው ያሸበረቁ ወለል ላይ የሚደርስ ርዝመት ያላቸው ቀሚሶች ናቸው። ምንም እንኳን ሁሉም ጎሳዎች የራሳቸው ሀገር በቀል ሙዚቃ ቢኖራቸውም ቡጋንዳ በኡጋንዳ ያለውን የሙዚቃ ቦታ ተቆጣጥሯል። የቡጋንዳ ሙዚቃ በዋነኛነት ከበሮ እና ሌሎች የከበሮ መሳሪያዎች ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ በአንዳንድ ውስብስብ ዳንሶች ይታጀባል። የምስራቅ ባጎሳ ጎሳዎች ከሳክስፎን ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሳሪያዎችን ይጫወታሉ። በሰሜን የሚገኙት አቾሊ እና ላንጊ ጎሳዎች ፒያኖ ይጫወታሉ። በምዕራብ የባንያንኮሬ የከበሮ ሙዚቃ በጣም የበላይ ነው፣ እና ከቡጋንዳ የበለጠ ግርማ ሞገስ ያለው ነው። ሙዚቃ እና ውዝዋዜ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚታዩ ቢሆንም ባህላዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜዎች በካምፓላ ማግኘት ቀላል ነው። ቢሆንም በሁሉም ክልሎች ማግኘትም ይቻላል።

### ደቡብ ሱዳን

ደቡብ ሱዳን የምስራቅ አፍሪካ የጥበባት እና የባህል ፌስቲቫል የልኡክ ቡድን ከላኩና ከተሳተፉ አገራት መካከል አንዷ ነች። አብዛኛዎቹ ደቡብ ሱዳናውያን በስደትም ሆነ በዲያስፖራ ነዋሪነት ከአገራቸው ውጪ ሆነውም የአካባቢያቸውን ባህል በመጠበቅ እረገድ አስኳል ሆነው እንዳሉ ይነገርላቸዋል። በአገሪቱ ባህል በከፍተኛ ደረጃ የተከበረ ሲሆን የአንድን ብሄር አመጣጥ እና ቋንቋ ለማወቅ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራበታል። የሚነገሩት የጋራ ቋንቋዎች ጁባ አረብኛ እና እንግሊዝኛ ቢሆኑም ሀገሪቱ ከምስራቅ አፍሪካ ጎረቤቶቿ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማሻሻል ኪስዋሂሊ ከሕዝቡ ጋር ለማስተዋወቅ እቅድ እንደያዘች ይነገራል።

ደቡብ ሱዳን የተለያዩ አገር በቀል ባህሎቿን የሚያንፀባርቅ የባህል ሙዚቃ ባህል አላት። ለምሳሌ የዲንቃ ሕዝቦች ባሕላዊ ሙዚቃዎች በጣም የተወደዱ ግጥሞችን ይታወቃሉ። አዛንዴዎች ግን በተለይ በተረት ታሪክ ይታወቃሉ።

በጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ እና በዘለቀው የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት የሙዚቃ ባህሉ በደቡብ ሱዳን አጎራባች አገሮች ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። በርካታ ደቡብ ሱዳናውያን ወደ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ እና ዩጋንዳ ተሰደዱ፤ ከዜጎች ጋር በመገናኘት ቋንቋቸውንና ባህላቸውን ተምረዋል። በአገሪቷ ከቀሩት፣ የሱዳን አካል በነበረችበት ጊዜ፣ ወይም ወደ ሰሜን ከሄዱት ሱዳን ወይም ግብፅ ከሄዱት መካከል አብዛኞቹ የጎረቤቶቻቸውን የአረብኛ ባህልና ቋንቋ አዋህደው ነበር። ከደቡብ ሱዳን የመጡ ብዙ ሙዚቀኞች እንግሊዝኛ፣ ኪስዋሂሊ፣ ጁባ አረብኛ፣ የአካባቢ ቋንቋቸው ወይም የቋንቋ ቅይጥ ይጠቀማሉ።

በ1970ዎቹ እና 1980ዎቹ ጁባ የበለፀገ የምሽት ሕይወት መኖሪያ ነበረች። ከፍተኛ የሀገር ውስጥ ባንዶች ስካይላርክስን እና ረጃፍ ጃዝን ያካትታሉ። ተወዳጁ አርቲስት ኢማኑኤል ከምቤ ሕዝብን፣ ሬጌን እና አፍሮቢትን እየዘፈነ ነው። እኤአ ዳይናሚክ በሬጌ ልቀቶቹ ታዋቂ ነው፣ እና ኢማኑኤል ጃል የዓለም አቀፍ ዝና የሂፕ ሆፕ አርቲስት ነው። ደቡብ ሱዳን እስካሁን ያፈራቻቸው ጥቂት ሴት አርቲስቶችም አሉ።

### ብሩንዲ

ብሩንዲ የምስራቅ አፍሪካ የጥበባት እና የባህል ፌስቲቫል የልኡክ ቡድን ከላኩና ከተሳተፉ አገራት መካከል አንዷ ነች። ዕደ ጥበብ በቡሩንዲ ውስጥ ጠቃሚ የጥበብ ስራ ሲሆን ለብዙ ቱሪስቶች ማራኪ ስጦታዎች ሆነው ያገለግላሉ። ሽመና ለሀገር ውስጥ የእጅ ባለሙያዎች የታወቀ የእጅ ሥራ ነው። እንደ ጭምብል፣ ጋሻ፣ ሐውልት እና የሸክላ ሥራ ያሉ ሌሎች የእጅ ሥራዎች በቡሩንዲ እውቅና አላቸው።

በቡርንዲ ከሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ ከበሮ መምታት የባህል ቅርስ አስፈላጊ አካል ነው። በዓለም ታዋቂ የሆኑት የብሩንዲ ሮያል ከበሮ መቺዎች፣ ከ40 ዓመታት በላይ የተጫወቱት፣ ካሪንዳ፣ አማሻኮ፣ ኢቢሺኪሶ እና ኢኪሪያንያ ከበሮዎችን በመጠቀም በባሕላዊ ከበሮ በመጫወት ይታወቃሉ። ዳንስ ብዙውን ጊዜ ከበሮ ትርኢት ጋር አብሮ ይሄዳል ፤ይህም በበዓላቶች እና በቤተሰብ ስብሰባዎች ላይ ብዙ ጊዜ ይታያል። በኦፊሴላዊ ሥነ ሥርዓቶች እና የአምልኮ ሥርዓቶች ላይ የሚካሄደው አባቲምቦ እና በፍጥነት የሚካሄደው አባናያጋሲምቦ ከታዋቂ  የብሩንዲ ዳንሶች መካከል ናቸው። አንዳንድ የሙዚቃ መሳሪያዎች ዋሽንት፣ ዚተር፣ ኢኬምቤ፣ ኢንዶኖንጎ፣ ኡሙዱሪ፣ ኢናንጋ እና ኢንያጋራ  በመባል ይታወቃሉ።

### ሱማሊያ

ሱማሊያ የምስራቅ አፍሪካ የጥበባት እና የባህል ፌስቲቫል የልኡክ ቡድን ከላኩና ከተሳተፉ አገራት መካከል አንዷ ነች። ሶማሊያ ታሪካዊ ቦታዎችን፣ የባህር ዳርቻዎችን፣ ፏፏቴዎችን፣ የተራራ ሰንሰለቶችን እና ብሔራዊ ፓርኮችን ያቀፉ በርካታ የአካባቢ መስህቦች አሏት። የቱሪስት ኢንዱስትሪው የሚቆጣጠረው በብሔራዊ የቱሪዝም ሚኒስቴር ነው። ራሳቸውን የቻሉት ፑንትላንድ እና ሶማሌላንድ ክልሎች የራሳቸው የቱሪዝም ቢሮ አላቸው። የሶማሌ ቱሪዝም ማኅበር (ሶምቲኤ) በብሔራዊ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዙሪያ ከአገር ውስጥ የማማከር አገልግሎት ይሰጣል።  እኤአ ከማርች 2015 ጀምሮ የደቡብ ምዕራብ ግዛት የቱሪዝም እና የዱር አራዊት ሚኒስቴር ተጨማሪ የጫካ ክምችቶችን እና የዱር እንስሳትን ክልል ለማቋቋም እቅድ መያዙን አስታውቋል።

ሶማሊያ በባህላዊ የሶማሌ ወግ ላይ ያማከለ የበለጸገ የሙዚቃ ቅርስ አላት። አብዛኞቹ የሶማሌ ዘፈኖች ፔንታቶኒክ ናቸው። ያም ማለት እንደ ዋናው ሚዛን ከሄፕታቶኒክ (ሰባት ኖት) ሚዛን በተቃራኒ በአንድ ኦክታቭ አምስት እርከኖችን ብቻ ይጠቀማሉ። የሱማሌ ሙዚቃ በስህተት እንደ ኢትዮጵያ፣ ሱዳን ወይም አረብ ባሕረ ገብ መሬት ባሉ ክልሎች ድምፆች ሊታወቅ ይችላል፣ ግን በመጨረሻ በራሱ ልዩ ዜማዎች እና ዘይቤዎች መለየት ግን ይቻላል። የሶማሌ ዘፈኖች አብዛኛውን ጊዜ በግጥም ደራሲዎች (ሚድሆ)፣ በዘፈን ደራሲዎች (ላክሳን) እና በዘፋኞች (ኮድካ ወይም “ድምፅ”) መካከል ያሉ የትብብር ውጤቶች ናቸው።

### እንደ መውጫ

የባህልና ስፖርት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ አለማየሁ እንደሚሉት ባህልና ጥበባት ሰዎች እርስ በርስ በሚኖራቸው ግንኙነት እና የማኅበራዊ መስተጋብር ለዘመናት ያፈሯቸውን እሴቶች እና የአኗኗር ዘይቤዎች ለአካባቢያቸው እና ለሌሎች ሕዝቦች የሚያጋሩበት እና የሚያስተዋውቁበት አንደኛው መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም ባህልና ጥበባት ለሀገረ መንግሥት ግንባታ እና ማሕበራዊ ሀብት ክምችት (Social Capital development) ያለው አስተዋጽዖ ከፍተኛ መሆኑ በተለያየ ጥናቶች የተረጋገጠ ነው፡፡ በመሆኑም  ብዝሃ ባህል እና እሴቶች ለተጀመረው የሀገረ መንግሥት ግንባታ ያላቸውን ሚና ለማጎልበት የጥበባትና ባህል ፌስቲቫሎች መዘጋጀት እና መሰል ሁነቶች በስፋት በማቀድ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ጥበብ ለማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲሁም ለህዝቦች ትስስር ሀይል (soft power) በመሆኑ ይህንኑ ፀጋ በመጠበቅ፣ ማልማትና ጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ሳምንቱን በታሪክ

# በሮም አደባባይ የታየው የኢትዮጵያ ጀግንነት

**ዋሰልኝ አየለ**

የኢትዮጵያውያን የጀግንነት ታሪክ በአገራቸው ብቻ የተወሰነ አይደለም። በጠላት አገር አደባባይ እንደ አንበሳ ሞገሳቸውን የሚያሳዩ ናቸው። ከ84 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሰኔ 7 ቀን 1930 ዓ.ም ኢትዮጵያዊው ጀግና ዘርዓይ ደረስ በጣሊያን ሮም አደባባይ የጣሊያንን ሕዝብ አፍ ያስያዘ የጀግንነት ገድል ፈጽሟል። በተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ የተጻፈው «የኢትዮጵያ ታሪክ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ - ከወልወል እስከ ጎንደር (ግንቦት 1927 - ኅዳር 1934)» መጽሐፍ እና ሌሎች ሰነዶችን ዋቢ አድርገን በዛሬው የሳምንቱ በታሪክ ዓምዳችን ይህን ክስተት እንዘክራለን።

ዘርዓይ ደረስ የተወለደው በ1908 ዓ.ም ኤርትራ ውስጥ አዲ ሓይስ በተባለ ስፍራ ነው። ያደገው ደግሞ እዚያው ኤርትራ ውስጥ ሓዘጋ በተባለ ቦታ ነው። ርዕሰ ደብር እቁበ እንድርያስ (በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች እየተዘዋወሩ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክና ትምህርት የተማሩና ያስተማሩ) በተባሉ የሃይማኖት አባት አማካኝነት የቤተ ክህነት ትምህርት ተምሯል።

ከቤተ ክህነት ትምህርት በኋላ ዘርዓይ አስመራ ከተማ ውስጥ በሚገኝና በሳልሳዊ ኢማኑኤል ስም በተሰየመ ትምህርት ቤት ገብቶ ዘመናዊ ትምህርት ተምሯል። ከዚያም መምህር ሆኖ ማስተማር ጀመረ። ይሁን እንጂ ዘርዓይ ለተማሪዎቹ ስለኢትዮጵያ ደጋግሞ መናገሩና መከራከሩ ለጣሊያኖቹ ምቾት የሚሰጥ ስላልነበር ከስራው ተባረረ። እርሱ ግን «ገብረሚካዜላውያን» የሚባል ማኅበር አቋቁሞ ኢትዮጵያ በጠላት እጅ ስለወደቀች ሁሉም ሰው በጸሎትም በመንፈስም ከኢትዮጵያውያን ጎን እንዲቆም መቀስቀስ ጀመረ። የኢትዮጵያን መወረር ተቃውሞ በጋዜጣ ላይ ገለጸ።

ከአንድ የኤርትራ ገዢ ዘንድ ቀርቦ ሲጠየቅ አማርኛ፣ ትግርኛ፣ ጣሊያንኛና አረብኛ መናገር እንደሚችልና ኦሮምኛ፣ ሶማሊኛና አገውኛ የሚያስጠናው ቢያገኝ መማር እንደሚፈልግም ተናገረ። አገረ ገዢውም እንዲህ ዓይነቱን ሰው አስመራ ውስጥ ከማስቀመጥ ወደ ኢጣሊያ መላክ የተሻለ እንደሆነ በማመኑ፤ ዘርዓይ በመስከረም 1929 ዓ.ም ወደ ሮም ተላከ። በዚያም አንድ የቅኝ ግዛት አገር ዜጋ ሊያገኘው የሚገባው ከፍተኛ ደረጃ ተሰጥቶት የአስተርጓሚነት ስራውን ጀመረ። ይሁን እንጂ ያ ሁሉ ስጋዊ ምቾቱ ለኢትዮጵያ ነፃነት ከመታገል ሊያግደው አልቻለም።

ሰኔ 7 ቀን 1930 ዓ.ም የኢጣሊያ መንግሥት በዶጋሊ ጦርነት ለሞቱት ጣሊያናውያን የተሰናዳ የመታሰቢያ መርሃ ግብር በሮም ከተማ በአንድ የመንግሥት አደባባይ ላይ አዘጋጅቶ ነበር።

ጥር 18 ቀን 1879 ዓ.ም የራስ አሉላ (አባ ነጋ) ጦር የኢትዮጵያን ድንበር ጥሰው የመጡትን ጣሊያኖችን ዶጋሊ በተባለ ቦታ ላይ ገጥሞ የጣሊያን ጦር አሰቃቂ ሽንፈት ገጥሞታል። ጣሊያን ለዚህ ክስተት ነበር መታሰቢያ ያዘጋጀች።

ዘርዓይ በዕለቱ ፒያሳ ዲ ፒአሞንቲ በተባለው አደባባይ እንዲገኝ የተደረገው የኢትዮጵያን የጦርና ሌሎች ዕቃዎች ይዞ ለማላገጫነት እንዲቆም ነበር። ዘርዓይ ከያዛቸው እቃዎች መካከል አንዱ ራስ አሉላ ዶጋሊ ላይ ጀብዱ የሰሩበትና በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ወቅት ከኢትዮጵያ ተዘርፎ የተወሰደው ጎራዴ ነበር። ዘርዓይም እቃዎቹን ይዞ እንዲሄድ ከመታዘዙ በቀር ለመሳለቂያነት መቆም እንዳለበት አልተነገረውም ነበር።

ዘርዓይ ፒያሳ ዲ ፒአሞንቲ አደባባይ ሲደርስ እንግዳ ነገር ተመለከተ። ቀደም ሲል አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተተክሎ የነበረው የይሁዳ አንበሳ ሐውልት ሮም አደባባይ ላይ ተተክሎ አየው። ከሐውልቱ ላይ ሁለት ግልገሎች የምታጠባ የተኩላ ምስል ተቀምጦበታል። በአንበሳው መስቀል ላይ ደግሞ የኢጣሊያ ባንዲራ ተሰቅሏል። የኢትዮያ ሰንደቅ ዓላማ መሬት ላይ ተጥሏል። በዙሪያው ተጽፈው ከሚታዩና የኢትዮጵያንና የሕዝቦቿን ክብር ከሚነኩ መፈክሮች መካከል አንዱ « ... የይሁዳ አንበሳን ልጆችሽ እንደፍየል ጭራውን ጠምዝዘው አምጥተው ከእግርሽ ስር ያሰግዱታል ...» የሚል ነበር። በአደባባዩ የተሰበሰበው ሕዝብም እየሳቀና እየጮኸ አንበሳው ላይ ምራቁን በመትፋት ያፌዝና ይሳለቅ ነበር።

> **ዘርዓይ ይህን ሁሉ ሰርቶ፤ በስድስት ጥይት ተመትቶ መትረፉ ጣሊያኖችን አበሳጫቸው፤ አስደነገጣቸውም።በወቅቱ በሮም ከተማ ውስጥ ከነበሩት ሐኪም ቤቶች ሁሉ የተሻለ ወደሚባለው የሕክምና ተቋም (ቀዳማዊ ኡምቤርቶ ፖሊክሊኒክ) አስገቡትና ሕክምና ተደርጎለት አገገመ**

ዘርዓይ ደረስ ሁኔታውን በመገረምና በመናደድ ስሜት ሲመለከት ማርሻል ማሪዮ ኢሶን የተባለ የዘበኞች አለቃ ወደ ዘርዓይ ቀርቦ ድርጊቱን መመልከት እንደማይችል ነገረው። በተጨማሪም ማርሻል ኢሶን የዘርዓይን መናደድ ስለተመለከተ ዘርዓይን ከአካባቢው ሊያባርረው ሞከረ። ዘርዓይ «እናንተ የምታዩትን እኔ የማላይበት ምን ምክንያት አለ?!» ብሎ ጠየቀው። የዘበኞቹ አለቃም የዘርዓይን ጥያቄ እንደድፍረት በመቁጠር « ... ከእንግዲህ አንበሳ የለም! ለተኩላዋ ልትሰግድና ልታመልካት ይገባሃል!» አለው። ዘርዓይ ግን «አይደረግም!» አለ። ክርክሩ ከረረ። ማርሻል ኢሶን « ... ከእንግዲህ በኋላ አንበሳው የተኩላዋ አሽከር መሆኑን ልነግርህ እወዳለሁ ... ያውም ንጽሕናውን ያሻሽል እንደሆነ ... » አለ። ዘርዓይ በእልህ ተከራከረ። አንበሳው ጣሊያኖችን ከአንድም ሁለት ጊዜ ሰባብሮ ድራሻቸውን እንዳጠፋቸው አስረዳው። የዘበኞቹ አለቃ « ... ከአንበሳው ጀርባ ላይ ወጥታችሁ አሳዩት ቁርጡን ይወቀው!» የሚል ትዕዛዝ ለወታደሮቹ ሰጠ። ሕዝቡ ጭምር አንበሳው ላይ ለመውጣት ተተረማመሰ።

ዘርዓይ ደረስ ስራውን የጀመረው በዚህ ሰዓት ነበር። በያዘው ጎራዴ ጣሊያኖችን መጨፍጨፍ ጀመረ። « ... ከእንግዲህ በኋላ አንበሳው የተኩላዋ አሽከር መሆኑን ማመን አለብህ ... ተኩላዋን ልታመልካት ይገባሃል ...» ብሎ ያፌዘበትን ማርሻል ኢሶንን ለአንበሳው እንዲሰግድ አድርጎ እጅና እግሩን ክፉኛ አቆሰለው። የሌሎችንም ሬሳ በአንበሳው ስር ጎተተው። ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ እንኳ ለመሸሽ አልፈለገም። ሮም ተሸበረች። «ኢትዮጵያ ሰብራ ገባታ የኢጣሊያን ሕዝብ ጨፈጨፈችው ... ታጥቀህ ራስህን ተከላከል ...» ተብሎ ታወጀ። ሁሉም በያለበት ተኩስ ከፈተ። በዘርዓይ ጎራዴና በአደባባዩ ላይ በነበረው ትርምስ ምክንያ ከሞተው ሰው በተጨማሪ « ... ታጥቀህ ራስህን ተከላከል ...» ተብሎ በታወጀው አዋጅ ምክንያት ብዙ ሰው እርስ በእርሱ ተጋደለ። የኢጣሊያ መንግሥት ባለሥልጣናት ድርጊቱ ውርደት ስለሆነባቸውና ነገሩን በምስጢር ስለያዙት ስንት ሰው እንደሞተ በውል አይታወቅም። አንዳንድ የታሪክ ጸሐፊዎች በዕለቱ በጥቂቱ የአምስት ሰዎች አስከሬን ከአደባባዩ ላይ መነሳቱን ሲጽፉ ሌሎች ደግሞ ቁጥሩን እስከ 18 ያደርሱታል። በትርምሱ ምክንያት ብዙ ሰዎች መቁሰላቸው የታሪክ ጸሐፊዎቹን አስማምቷል።

ዘርዓይ ጣሊያኖች ላይ እርምጃ መውሰድ የጀመረው ከረፋዱ አራት ሰዓት አካባቢ ነበር። ሽብሩ ግን እስከ 10 ሰዓት ተኩል ድረስ ቀጥሎ ነበር። ከቀኑ 10 ሰዓት ተኩል አካባቢ አገሪቱ ሰላም መሆኗንና ሽብሩ የተፈጠረው አንድ የአዕምሮ በሽተኛ ህመሙ ተነስቶበት እንደሆነ የሚገልፅ አዋጅ ተነገረ። የአወጁ ቃል ይህ ብቻ አልነበረም። « ... ወደ ፒያሳ ሄዳችሁ እጁን ያዙ!» የሚል ትዕዛዝም ነበረው። በዚህ ትዕዛዝ ምክንያት የከተማው ሕዝብ እንደገና ወደ አደባባዩ ወጣ።

ዘርዓይ ደረስ ሰውነቱ እንደነብር ተቆጣ። በተኩላዋ ሐውልት ላይ ቆሞ በመናገር ሕዝቡን ዝም አሰኘው። « ... በየቤታችሁ እየዞርኩ ብዙ ሰው አርድ ነበር። ግን እኔን አስሮ የያዘኝና እዚህ ሲያኮራምተኝ የዋለው የአንበሳው ፍቅር ነው።ደግሞም አሟሟቴ ከአንበሳው ስር እንዲሆንልኝ ፈልጌ ነው። ወንድ ይምጣና ይማርከኝ ...» ብሎ ተናገረ። ከተኩላዋ ላይ ወርዶ አንበሳውን እየዳሰሰ ቆመ።

አውቶማቲክ መሳሪያ የያዙ ወታደሮች በሞተር ሳይክል፣ ከሁለት አቅጣጫ በመምጣት ዘርዓይን ተኩሰው መቱት። ጎራዴውን መዘዘና እንደገና ወደ ሕዝቡ ገሰገሰ። ከተማዋ በተኩሱና በሽሽቱ ምክንያት እንደገና ተረበሸች። ዘርዓይ ቢወድቅም ሊቀርበው የደፈረ ሰው አልነበረም። ጎራዴውን ይዞ ከወደቀበት ተነሳ። መሬት ላይ ወድቆ የነበረውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በማንሳት በደሙ ለውሶ አንበሳው ላይ ሰቀለው። ተኩላዋ ላይ የነበረውን የኢጣሊያ ባንዲራ የተሰበሰበው ሕዝብ እያየው አወረደው፤ ቀዳዶ ከመሬት ጣለውና ረገጠው። አንበሳውን እየሳመ ያነጋግረው ነበር። ዘርዓይ ይህ ሁሉ ሲያደርግ ሊያስቆመው የሞከረ ሰው አልነበረም። አሁን ግን ወታደሮቹ ደግመው ተኮሱበት። ዘርዓይም ወደቀ ግን አልሞተም ነበር።

ዘርዓይ ይህን ሁሉ ሰርቶ፤ በስድስት ጥይት ተመትቶ መትረፉ ጣሊያኖችን አበሳጫቸው፤ አስደነገጣቸውም። በወቅቱ በሮም ከተማ ውስጥ ከነበሩት ሐኪም ቤቶች ሁሉ የተሻለ ወደሚባለው የሕክምና ተቋም (ቀዳማዊ ኡምቤርቶ ፖሊክሊኒክ) አስገቡትና ሕክምና ተደርጎለት አገገመ። ሐምሌ 15 ቀን 1930 ዓ.ም ቤኒቶ ሙሶሊኒ በዘርዓይ ጥቃት የቆሰሉትን ለመጠየቅ ሐኪም ቤት ሲደርስ ማርሻል ማሪዮ ኢሶን ሞቶ እየተገነዘ ነበር። ለኢሶን ያመጣለትን ኒሻን አስቀምጦ በከፍተኛ ቁጣ ዘርዓ ወደተኛበት ክፍል ገባ። አገግሞ ስላገኘው የበለጠ ተናደደ። « ... አንተ ነህ ሮምን የደፈርካት?» ብሎ ጠየቀው። ሙሶሊኒም ዘርዓይ በሚገባ ታክሞ እንዲድን ለሐኪሞቹ አደራውን ሰጠ። ዘርዓይን በሞት መቅጣት የኢጣሊያን ስም በማይረባ ነገር በመላው ዓለም መበተን መሆኑን ገልፆ፤ በዳኝ ጊዜ በቃልም በጽሑፍም ይቅርታ እንዲጠይቅ፣ የአዕምሮ ሕመምተኛ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ እንዲዘጋጅና ዘርዓይም ሕመምተኛ መሆኑን እንዲያምን እንዲደረግ ትዕዛዝ ሰጠ።

ፕሮፌሰር ፋውስቶ ኮንስታንቲኒ የተባለው ሐኪም የሙሶሊኒን ትዕዛዝ ለማስፈፀም ላይ ታች አለ። ለብዙ ቀናት አግባብቶ አንድ ወረቀት እንዲፈርም አቀረበለት። ደብዳቤው ስለተደረገለት ሕክምና አመስግኖ « በ500 ወታደሮች አደባባይ ላይ በድንገት ታምሜ በሰዎች ሕይወት ላይ ስላደረስኩት በደል ይቅርታ እጠይቃለሁ። በስድስት ጥይቶች የተመታው ሰውነቴና አንጎሌም ድኖ በቅርብ ቀን ለመውጣት ሀኪሙ ተስፋ ሰጥቶኛል ...» የሚሉ ሃሳቦችን ያካተተ ነበር። ዘርዓይ ደብዳቤውን ከሐኪሙ ነጥቆ በመቀዳደድ ፊቱ ላይ በተነበት። ቀደም ሲል ስለዚሁ ጉዳይ በተደረገ ክርክር ላይ ዘርዓይ « ... በእናንተ አፍ እውነት የሚነገረው መቼ ይሆን?» ብሎ በድፍረት የጠየቀው ፕሮፌሰር ኮንስታንቲኒ የሐፍረት ማቅ ለብሶ ወጣ፤ ድጋሚ ወደ ዘርዓይ አልተመለሰም።

ፕሮፌሰር ኮንስታንቲኒ በድጋሜ እርሱ በአካል ወደ ዘርዓይ ባይመለስም ጥረቱን ግን አላቋረጠም ነበር። ሁለት ኢትዮጵያውያንን (አንድ ስማቸው ያልተጠቀሰ ደጃዝማችና አንድ መነኩሴ) ላከበት። ሁለቱ ሰዎች የዘርዓይን አቋም ለማስለወጥ ብዙ ደከሙ። የኢጣሊያን መንግሥት ኃያልነትና የእርሱን ወጣትነት እያገናዘቡ ብዙ አባበሉት። እርሱ ግን ሀሳቡን መለወጥ አልፈለገም። ወደ ደጃዝማቹም ዞሮ « ... እንደርስዎ ያለ ሰው የማንም ጭነት ማጓጓዣ መሆን አልነበረበትም» አላቸው። በተጨማሪም « ለእነርሱ ክብርና ለእነርሱ ወረራና መስፋፋት ከቶ የእናንተ አጠንጣኝነት ምንድን ነው? ሲል ጠየቃቸው። ደጃዝማቹ ግን መልስ አልነበራቸውም። ዘርዓይ ቀጥሎም «እንስሶች እንኳ ጌታቸውን ይወዳሉ። እናንተ ግን ቅሌታችሁን ተሸክማችሁትዞራላችሁ!»ብሏቸው ወደ መነኩሴው ዞረ። «የእግዚአብሔር እንደራሴ መስለው በጥቁር ጨርቅ ትምነሸነሻላችሁ። የሰውን የእኩልነት ኑሮ ለማጥፋት ከላይ ተልካችሁ የመጣችሁ መውሰፍቶች ናችሁ! ቅስናዎን ይተውት! ተራ መሐይም መስለው እንደሌሎች ባንዳዎች ቢያገለግሉ ይሻላል፤ ከአጠገቤ ውጡ!» ብሎ አባረራቸው። ዘርዓይ አቋሙን እንደማይቀይር ስለታወቀ በድጋሚ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ አልቀረበለትም።

አንድ ጊዜ መደበኛ ፍርድ ቤት ሌላ ጊዜ የጦር ፍርድ ቤት ሲያመላልሱት ቆይተው ታሰረ፤ በዚያው በእስር ቤት እያለ በ1937 ዓ.ም ሕይወቱ አለፈ። አስከሬኑም ወደ ኤርትራ መጥቶ በሐዘጋ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንዲያርፍ ተደርጓል።

እነሆ ይህን ጀግና ታሪክ ሲዘክረው ይኖራል!

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

# የቋንቋን ድንበር የሰበረው ወጣት

## ድምጻዊ - ዳዊት ነጋ



ድምፃዊ ዳዊት ነጋ፣

አቤል ገ/ኪዳን

ሳምንቱ ለሙዚቃ አፍቃሪው ህብረተሰብ አሳዛኝ ነበር፡፡ በትግርኛ ሙዚቃዎቹ የሚታወቀው እና ከፍተኛ ተወዳጅነት ያተረፈው ድምጻዊ ዳዊት ነጋ ባልተጠበቀ ሁኔታ ለህክምና በሄደበት ክሊኒክ በድንገት ማረፉ መሰማቱ መላው ኢትዮጵያውያንን አስደንግጧል። እሁድ አመሻሽ ላይ የተሰማው ዜና እንኳን ለሌላው ሕዝብ ይቅርና ዳዊትን በቅርብ ለሚያውቁት እንኳን ያልተጠበቀ ዱብእዳ የሆነ ነበር፡፡ ከእረፍቱ ዜና መሰማት በኋላ የወጡ ፎቶዎች እንደሚያሳዩት ድምጻዊው ክሊኒክ ውስጥ ከሕክምና ባለሙያዎች ጋር ሲነጋገር የሚያሳይ ፎቶ በወቅቱ ደህና እንደነበር የሚያሳይ ሲሆን የሞቱ ዜና አስደንጋጭ የሆነውም በዚህ የተነሳ ነው፡፡ የሆነ ሆኖ ለሞት ያበቃው ህመም ምን እንደነበር ወደፊት ሊታወቅ የሚችል ጉዳይ ሆኖ ዜና እረፍቱ ግን አሳዛኝ እና ልብ ሰባሪ ነበር፡፡

ዳዊት የመቐለ ተወላጅ ነው፡፡ የልደቱ ቀንም ሚያዝያ 2 /1980 ዓ.ም ነው፡፡ በሙዚቃ ቪዲዮዎቹ ላይ ድንቡሽቡሽ ብሎ ሲታይ ከደህና ቤተሰብ የተወለደ የሚመስለው ዳዊት ሀቁ ግን ወላጆቹን ገና በ10 ዓመቱ አጥቶ በብዙ መከራ ተፈትኖ ያደገ ልጅ ነበር፡፡ ከወላጆቹ እረፍት በኋላ ዳዊት የኖረው እማማ ታደሰች የሚባሉ የእናቱ የልብ ወዳጅ የነበሩ ጎረቤት ጋር ነበር፡፡ በኋላ ላይ ደግሞ ቤት ተከራይቶ መኖር ጀምሮ ነበር፡፡ በወቅቱ ለቤት ኪራይ 200 ብር ይከፍል የነበረ ሲሆን እሱን መክፈል ቀላል አልነበረም፡፡ በዚህም የተነሳ ኪራይ ገንዘብ አልሞላ ሲለው አንዳንዴ በእኩለ ሌሊት በአጥር ዘልሎ እየገባ ሌላ ጊዜ ጓደኞቹ ጋር እያደረ ሲሳካለትም ኪራዩን እየከፈለ ኑሮውን ገፋ፡፡ በወቅቱ ስለነበረው አኗኗር ሲናገር "ሲጋራ እሸጥ ነበር፡፡ መቀሌ ውስጥ የሚሸጠውን ነገር ሁሉ ሸጫለሁ" ይላል፡፡

ዳዊትና ሙዚቃ የተዋወቁት ገና በልጅነት ነው። ከልጅነቱ ጀምሮ ለሙዚቃ ጥልቅ ፍቅር እንዳደረበት የሚናገረው ዳዊት በ15 ዓመቱ አካባቢ የሙዚቃ ፍላጎቱን እና ህልሙን እውን ማድረግ በማሰብ "ሰርከስ ትግራይ" በሚባለው የሰርከስና ሙዚቃ ቡድንን በዘፋኝነት ለመቀላቀል ጥያቄ አቀረበ። ጥያቄው በጊዜ መልካም ምላሽ ባያገኝም ወደ ማርሽ ባንድ እንዲቀላቀል እና ከበሮ (ድራም) እንዲጫወት እድል ተሰጠው። ለሰባት ዓመታት ገደማ የማርሽ ባንዱ ድራመር በነበረበት ጊዜ ሁሉ ግን በውስጡ ዘፋኝ የመሆን ፍላጎት እና ህልም ስለ ነበረው ለመዝፈን ከመሞከር አላቆመም። ይህ ህልሙም በመጨረሻ ተሳካና ከሕዝብ ጋር ያገናኘውን ባባኢለን የተሰኘ ሙዚቃ ተጫወተ፡፡ ሙዚቃው ከዳዊት አስገምጋሚ ድምጽ ጋር ፍጹም የተዋሀደ ፤ የትግርኛ ባህላዊ ሙዚቃ ለዛ ያልጠፋበት ፤ ዘመናዊነትን በልኩ የደረበ በመሆኑ እንኳን ትግርኛ በሚሰማው ሕዝብ ይቅርና ትግርኛ በማይሰማው ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተደማጭነት አገኘ፡፡ ከዚያን በኋላ የዳዊትን የስኬት ጉዞ የሚያስቆመው አልተገኘም፡፡ "ዳኣመና"፣ "ባባ ኢለን"፣ "ሕድያት መቀለ"፣ "ወዛመይ"፣ "ዘዊደሮ"፣ "ብነጸላይ"፣ "ቅዱስ ጸባያ" እና "ቸኮላታ" ዳዊት የታወቀባቸው ሙዚቃዎች ሆኑ። በተለይ ባባኢለን ፤ ወዛመይ ፤ ዘዊደሮ እና ብነጸላይ በጣም ከፍተኛ ተወዳጅነት አትርፈውለታል፡፡ እስካሁን በዩቲብ ባላቸው እይታ ብንመዝናቸው እንኳ ወዛመይ ከ19 ሚሊዮን በላይ ፤ ዘዊደሮ 8 ሚሊዮን ገደማ ፤ ባባኢለን ከ8 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ፤ ብነጸላ እንዲሁ ከ8 ሚሊዮን በላይ ተመልካች አግኝተዋል፡፡

ከዓመታት በፊት "ኦሮሚያ" በሚል ርዕስ በትግርኛ፣ ኦሮሚኛና በአማርኛ የሰራው ሙዚቃ ለአድናቂዎቹ ማድረሱም ይታወሳል። የዘፈኑ ይዘት አንድ ወጣት በአንዲት የኦሮሞ ኮረዳ ፍቅር መሸነፉን እንዲሁም ስለውበቷና ስለማንነቷ ይተርካል። ድምጻዊ ዳዊት፣ በ2011 አክሱማይት የተሰኘ የሙዚቃ ሰንዱቅ (አልበም) ወደ ሕዝብ አድርሷል። የመጨረሻው ነጠላ ዜማው "አጀኺ ትግራይ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሲሆን በጦርነቱ ምክንያት ስለተለያዩና መገናኘት ስላልቻሉ የትግራይ ቤተሰቦች ናፍቆት ገልጿል።

ዳዊት የሙዚቃ ከፍታው ላይ ይድረስ እንጂ ሕይወቱ ከባድ ነበር፡፡ ነገር ግን መንፈሰ ጠንካራ እንደሆነ ይናገራል። "እኔ ብቻ ሳልሆን ሁሉም ሰው ይፈተናል። ዋናው ነገር ይሄን ፈተና እንዴት አድርገህ ታልፈዋለህ የሚለው ጉዳይ ነው" ይላል ስላለፈው ሕይወቱ ሲናገር። አክሎም "ስኬት ቅርብ ነው ጠንካራ ከሆንክ" በማለትም ለወጣቶች ከሕይወት ልምዱ ያካፍላል፡፡ በእርግጥም ጠንካራ መሆኑ ብዙ አግዞት ከማርሽ ባንድ የተነሳው ወጣት ድምጻዊ በኮክ ስቱዲዮ አልበም ካወጡ ዝነኛ የደቡብ አፍሪካ እና አንጎላ አርቲስቶች ጋር ሙዙቃ እስከማቅረብ ደርሷል፡፡ ካሌብ ሾው በተሰኘ ፕሮግራም ላይ ቀርቦ ሰውን በሕይወት እያለ ስለማድነቅም ሲጠየቅ "ሰውን በሕይወት እያለ ነው ማመስገን ያለብን፡፡ እንኳን ለሀገር የሰራ ይቅርና የራስህ ሕይወት ያሸነፈ ሰው አድናቆት ይገባዋል፡፡ ማድነቅ መሰልጠን ነው፡፡" ብሎ ነበር፡፡ ድምፃዊ ዳዊት ነጋ ባለትዳርና የአንድ ልጅ አባት ነበር።

ከዜና እረፍቱ በኋላ የሙያ አጋሮቹ ማዘናቸውን በማሕበራዊ ሚዲያ የገለጹ ሲሆን ከነዚህም መሀከል የሙዚቃ ሀያሲው እና የአዲስ አበባ ባህል ፤ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ሃላፊ አቶ ሰርጸ ፍሬስብሀት "የወጣት፣ ያውም የትልቅ ባለተስፋ ጠቢብን የሕልፈተ ሕይወት አስደንጋጭ ዜና መስማት በጣም ያሳዝናል። ነፍስ ኄር "ብሷል፡፡ ድምጻዊ ሳሚ ዳን "ነብስ ይማር ወንድሜ፤ እረጅም የስኬት መንገድን ብንመኝም ፈጣሪ የፈቀደው ግን ሆኗል" ሲል ሌሎችም እንዲሁ ኀዘናቸውን ገልጸዋል። በርካታ ኢትዮጵያውያንም እንዲሁ ኀዘናቸውን በስፋት የገለጹ ሲሆን ሙዚቃው ትግርኛ ቋንቋን ሳይሰሙ እንኳ ይወዷቸው እንደነበር ገልጸዋል፡፡ የአርቲስቱ ሥርዓተ ቀብር ማክሰኞ ሰኔ 7 ቀን 2014 ዓ.ም በቅድስት ስላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል፡፡

# አባ ለታ

ወደኋላ ጥቂት ሄደው የሚያስታውሱ ሰዎች ያወቁታል፡፡ በተለይም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በሚያቀርባቸው የኦሮምኛ ድራማዎች ላይ ከሚታወቁ ዋነኛ ተዋንያን መሀከል አንዱ እሱ ነው፡፡ትወናው ኦሮምኛ ቋንቋን በማያውቁ ሰዎች ዘንድ ሁሉ ፈገግ የሚያሰኝ ጥበበኛ ነው፡፡አድማሱ ብርሃኑ! ጋዜጠኛ ጀሚል ይርጋ ስለእሱ ያሰፈረውን ጽሁፍ እነሆ አጋራናችሁ!

ብዙዎች በትወናው ያስታውሱታል፤ አድማሱ ብርሃኑ - ተዋናይ፣ ሙዚቀኛ፣ ተወዛዋዥ እና የሙዚቃ መሳሪያ (ትራምፔት) ተጫዋች የነበረ ታላቅ የጥበብ ሰው !ብዙዎች የሚጠሩት "አባ ለታ" በተሰኘው የመድረክ ስሙ ነው። አርቲስት አድማሱ ከአባቱ ከአቶ ብርሃኑ መገርሳና



ሁስገቡ የጥበብ ሰው አድማሱ ብርሃኑ፣

ከእናቱ ከወ/ሮ ዘነበች ጉሹ ሐምሌ 26 ቀን 1948 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን ቦጂ ቢርመጅ ወረዳ፣ በቢላ ከተማ ነው የተወለደው።

የትውልድ ቀዬውን ገና በትንሽነቱ ለቆ ኑሮውን ከአክስቱ ጋር ጦላይ በማድረጉ ፣ ትምህርቱንም እዚያው ጦላይ እስከ አራተኛ ክፍል፣ አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ ደግሞ በማታ ትምህርት እስከ ሰባተኛ ክፍል ተምሯል፡፡ ለጥበብ የነበረው ፍላጎት በማየሉ በ1968 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ቴአትርና ባህል አዳራሽ (ማዘጋጃ) በባህል ድምፃዊነት በመቀጠር አገልግሎት የጀመረ ሲሆን፣ በድምጻዊነቱም "ያ ቱሩንጎ" እና "ቢቂልቱ ገነማ" የተሰኙት ዘፈኖቹ ተወዳጅነት አትርፈውለታል። ለሂርዳ ጋንፉሬ፣ ዳግም መኮንን፣ አስቴር አብዲ፣ ሀብታሙ ለሙ እና ለሌሎችም የዘፈን ግጥሞችን አበርክቷል–ከዘፋኝነቱ በተጨማሪ።

በሀገር ፍቅር፣ በራስ ቴአትርና በብሔራዊ ቴአትር በታዩ ዕውቅ እና ተወዳጅ የመድረክ ተውኔቶችም ላይ ተውኗል። ከተጫወታቸው ቴአትሮች መካከልም "ቴዎድሮስ"፣ "ስመኝ ስንታየሁ"፣ "ባልቻ አባ ነብሶ"፣ "የቬኑሱ ነጋዴ"፣ "እሳት ሲነድ"፣ "መልዕክተ- ወዛደር"፣ መቅድም እና "የቆሰሉ ምሽጎች" ይጠቀሳሉ።

በአብዛኛው ህብረተሰብ ዘንድ ከፍተኛ ዕውቅናን ያገኘው እና ተወዳጅነትን ያተረፈው ግን የኢትዮድያ ቴሌቪዥን በኦሮምኛ ቋንቋ ሥርጭት ከጀመረ በኋላ ያስተላልፍ በነበረው "Dhangaa" የመዝናኛ ፕሮግራም ነው። በዚህ ዝግጅት ላይ ይታዩ በነበሩ ጭውውቶችና ድራማዎች ላይ ከነ አርቲስት ታደሰ ጩቄ፣ ሙሉጌታ ባልቻ፣ ሁምኔቻ አሰፋና ከሌሎችም ጋር በመሆን በደራሲነት፣ በአዘጋጅነትና በተዋናይነት ተሳትፏል። ከሁሉም በላይ ለ "Dhangaa" ዝግጅት መወደድ የነበረው አስተዋፅኦ ከማንም የበለጠ ነው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል። የኦሮምኛ ቋንቋን የማይሰሙ ሰዎች ሁሉ ፕሮግራሙን እንዲከታተሉ ያስቻለና አቅም የፈጠረ ሰው ነበር።

አሁን የኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኔትወርክ (OBN) ቀድሞ የ"ኦሮሚያ ቴሌቪዥን" ላይም በ "Dheebuu" እና በመሰል ድራማዎች ላይም ተውኗል። "ለኪነ ጥበብ የታመነ" እንደሆነና "ለቁሳዊ ጥቅሞች የማይንሰፈሰፍ" ሰው እንደነበር በቤተሰቦቹና በሥራ ባልደረቦቹ ጭምር የሚመሰከርለት ይህ ታላቅ የጥበብ ሰው፣ በድንገተኛ ሕመም የካቲት 7 ቀን 2008 ዓ.ም. ነበር ያረፈው። አርቲስት አድማሱ ባለትዳርና የሁለት ወንዶችና የሦስት ሴቶች ልጆች አባት ነበር፡፡

# ዓለም አቀፍ

## የዊክሊክስ መስራች ጁሊያን አሳንጄ ለአሜሪካ ተላልፎ ሊሰጥ እንደሚችል ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዊክሊክስ መስራች ጁሊያን አሳንጄ ለአሜሪካ ተላልፎ የመሰጠቱ ጉዳይ በዩናይት ኪንግደም የሀገር ውስጥ ሚኒስትር ፕሪቲ ፓቴል ተቀባይነት እንዳገኘ ተገለጸ። ጁሊያን አሳንጄ ውሳኔውን ይግባኝ ለማለት 14 ቀናት እንዳለውም የዩናይትድ ኪንግደም ሀገር ውስጥ ጽህፈት ቤት አስታውቋል።

ፍርድ ቤቶች ጁሊያን አሳንጄን አሳልፎ የመስጠት ጉዳይ “ከሰብዓዊ መብቱ ጋር የማይጣጣም” መሆኑን ቢገነዘቡም በአሜሪካ ውስጥ “በተገቢው ሁኔታ እንደሚስተናገድ” ማረጋገጣቸውን ገልጿል። ጁሊያን አሳንጄ እአአ 2010 እና 2011 አሹልኮ ባወጣቸው ሰነዶች ምክንያት በአሜሪካ ባለሥልጣናት ይፈለጋል። በዊክሊክስ የታተሙት እነዚህ ሾልከው የወጡት ሰነዶች ከኢራቅና አፍጋኒስታን ጦርነት ጋር የተያያዙ ናቸው ተብሏል።

የአውስትራሊያ ዜግነት ያለው ጁሊያን በለንደን ቤልማርሽ እስር ቤት የሚገኝ ሲሆን ተላልፎ ላለመሰጠትም ከፍተኛ ትግል አድርጓል። በሀገር ውስጥ ሚኒስቴር የተላለፈውን ውሳኔም በምላሹ ዊክሊክስ ይግባኝ እንደሚል አረጋግጧል። የጁሊያን ባለቤት ስቴላ በበኩሏ ባለቤቷ “ምንም ስህተት አልሰራም” እንዲሁም “ምንም ወንጀል አልሰራም” ስትል ተናግራለች ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

የጁሊያን ባለቤት ስቴላ በበኩሏ ባለቤቷ “ምንም ስህተት አልሰራም” እንዲሁም “ምንም ወንጀል አልሰራም” ስትል ተናግራለች። “ጋዜጠኛ እና አሳታሚ ነው እናም ስራውን በመስራት ብቻ ነው እየተቀጣ ያለው” ብላለች። የሚዲያ ኩባንያው ዊክሊክስ፣ ማንነታቸው ባልታወቁ የተሰጡ ሚስጥራዊና አወዛጋቢ መረጃዎችን ይፋ በማውጣት ይታወቃል።

በአውሮፓውያኑ 2019 በዩናይትድ ኪንግደም የዋስትና መብትን በመጣስ የእስር ቅጣት የተላለፈበት ሲሆን፤ በወቅቱም የአሜሪካ የፍትህ ዲፓርትመንት በዊክሊክስ የወጡ መረጃዎች ሕይወትን አደጋ ላይ የሚጥሉና የስለላ ሕጉን ጥሷል በሚል 17 ክሶችን አቅርቧል።

የአሳንጄ የጠበቆች ቡድን በበኩሉ ከኢራቅ እና አፍጋኒስታን ጦርነት ጋር በተገናኘ በዊኪሊክስ የታተሙ



ሚስጥራዊ ሰነዶች የአሜሪካን ጥፋት የሚያጋልጡ እና የሕዝብን ጥቅም ያስጠበቁ ናቸው ብሏል።

## በአሜሪካ የሚመራው ጥምር ኃይል የአይኤስ መሪን ሶሪያ ውስጥ መያዙ ተነገረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በአሜሪካ የሚመራው ጥምር ኃይል የጽንፈኛው እስላማዊ ቡድን አይኤስ ከፍተኛ መሪን ሰሜን ሶሪያ ውስጥ ባካሄዱት አሰሳ በቁጥጥር ስር ማዋላቸው ተነገረ። በቁጥጥር ስር የዋለው የእስላማዊው መንግሥት ቡድን መሪው "ከፍተኛ ልምድ ያለው ቦምብ ሰሪ እና የቡድኑ ዘመቻዎች አስተባባሪ” ነበር ሲል ጥምር ኃይሉ ባወጣው መግለጫ አመልክቷል፡፡

ባለሥልጣናት ለአሜሪካ መገናኛ ብዙኃን እንደተናገሩት የአይኤስ ቡድን ባለሥልጣን ነው የተባለው ግለሰብ ሃኒ አሕመድ አል-ኩርዲ በሚል ስም ይታወቃል። ግለሰቡን ለመያዝ የተደረገውን ዘመቻ ሲከታተል የነበረ ቡድን እንዳመለከተው በሁለት ሄሊኮፕተሮች የተጫኑ ወታደሮች ሶሪያ ከቱርክ ጋር በምትዋሰንበትና በተቃዋሚዎች ቁጥጥር ስር በምትገኘው አሌፖ አቅራቢያ ባለችው አል-ሁማይራ ውስጥ ተሰማርተው ነበር።

በአሰሳው ወቅት በጥምር ኃይሉ ወታደሮችና በታጣቂዎች መካከል ለሰባት ደቂቃ የቆየ የተኩስ ልውውጥ መደረጉንና



**የአሜሪካ መራሹ ኃይል ኢላማ የነበረውን ቤት የሚመለከት አንድ ልጅ**

የአይኤስ መሪውን ይዘው መሄዳቸውን ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ መቀመጫውን ያደረገው የሶሪያን ጉዳይ የሚከተታለው ቡድን አመልክቷል።

ወታደሮቹ የጽንፈኛውን ቡድን መሪ ከያዙ በኋላ በምሥራቃዊ አሌፖ ክልል ውስጥ በቱርክ የሚደገፉ አማጺያን ወዳሉበት ካምፕ እንደወሰዱትም ተገልጿል። አንድ የአል-ሁማያር መንደር ነዋሪ እንደተናገረው ወታደሮቹ ከአሌፖ ከተማ የተፈናቀሉ ሰዎች ይኖሩበታል ተብሎ ይታመን የነበረን አንድ ቤት ወረው ፈትሸዋል።

"ሄሊኮፕተሮቹ ከአካባቢው ከሄዱ በኋላ ወደ ቤቱ ሄደን ስንመለከት የታሰሩ ሴቶችና ሕጻናት ሜዳ ላይ አገኘን" ሲል ግለሰቡ ለፈረንሳይ ዜና ወኪል አዣንስ ፍራንስ ፕሬስ ገልጿል።

"ወታደሮቹ አንድ ሰው ይዘው የሄዱ ሲሆን፣ ሌሎቹ ወንዶች ግን የት እንደሄዱ አላወቅንም። ሴቶቹን ባገኘናቸው ጊዜም 'ፋዋዝን ይዘውት ሄደዋል' ሲሉ ሰምተናቸዋል" ብሏል። አሰሳው በጥንቃቄ የታቀደና የተፈጸመ በመሆኑ በሰላማዊ ሰዎች ላይ ጉዳት እንዳልደረሰ የጥምር ኃይሉ ባወጣው መግለጫ ላይ አመልክቷል።

ዋሽንግተን ፖስት የአሜሪካ ባለሥልጣናትን ጠቅሶ እንደዘገበው የተያዘው የአይኤስ መሪ አሕመድ ኩርዲ የተባለና "ዋሊ" ወይም የራቃ አስተዳዳሪ በሚልም ይታወቃል። ራቃ ከአሌፖ በስተምሥራቅ የምትገኝ ሲሆን እስላማዊ መንግሥት ወይም አይኤስ ከስምንት ዓመት በፊት ሰፊ ግዛትን ከሶሪያና ከኢራቅ ተቆጣጥሮ የራሱን ግዛት ሲያውጅ ራቃን ዋና ከተማው እንደሆነች አውጆ ነበር።

ቡድኑ ከሦስት ዓመት በፊት በጥምር ኃይሉ እና በሶሪያ ተቃዋሚ ኃይሎች ተገፍቶ አብዛኛውን ግዛቱን ተነጥቆ ተዳክሟል። ነገር ግን አሁንም በሁለቱ አገራት ውስጥ በስድስት ሺህ እና በ10 ሺህ የሚቆጠሩ ተዋጊ ኃይሎች እንዳሉትና የደፈጣ እንዲሁም የቦምብ ጥቃቶችን እንደሚፈጽም የተባበሩት መንግሥታት አመልክቷል።

ባለፈው የካቲት ወር የአሜሪካ ልዩ ኃይሎች ተመሳሳይ ዘመቻ ኢድሊብ ግዛት ውስጥ አድርገው የአጠቃላዩ የአይኤስ ቡድን መሪ የሆነውን አቡ ኢብራሂም አል-ሐሺሚ አል-ቁራይሺን መግደላቸው ይታወሳል።

ይህንንም ተከትሎ አይኤስ ምንም አይነት ዝርዝር ሳይሰጥ የተገደለበትን መሪውን የሚተካ ሌላ ግለሰብ መሰየሙን ገልጾ ነበር።


### የስም ማስታወቂያ

ዲቫይን ሲድ ኢንተርናሽናል ቸርች (DIVINE SEED INTERNATIONAL CHURCH) የተባለ የሃይማኖት ተቋም ምዝገባ ለማድረግ ያመለከተ በመሆኑ በዚህ ስያሜ እና ዓርማ ተቃውሞ ያለው አካል ካለ በ10 ቀን ወደ የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል እንዲቀርብ፡፡

**የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል**

### ደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር አዲስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0004288991 አማረ ገብሬ ነጩ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ንፋስ ስልክ ላፍቶ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የእጅ በእጅ ሽያጭ ተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ደረሰኝ ውስጥ ከቁጥር 251 እስከ 264 የተሰራበት እና ከ265 እስከ 500 ያልተሰራበት እንዲሁም የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ከ001 እስከ 0030 የተሰራበት እና ከ0031 እስከ 0250 ያልተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት ንፋስ ስልክ ላፍቶ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም አማረ ገብሬ ነጩ**

### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት ፍቅርተ አያሌው እና በፍ/ባለዕዳ እነ ፍሰሀ አበበ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 273220 በ21/10/2013 ዓ.ም እና በ21/10/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 የሚገኝ የጋራ መኖሪያ ቤት ህንፃ ቁጥር B069 የቤ.ቁ 069/29 ቦሌ ቡልቡላ ሳይት የሚገኝ የባንክ እዳ 229,828.45 ያለበት የግራ ቀኙ እግድ ያለበት የሆነው የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 418,740(አራት መቶ አስራ ስምንት ሺ ሰባት መቶ አርባ ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሀምሌ 18 ቀን 2014 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ8፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡
የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን፤ እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት ¼ኛውን በባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡
በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጉድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬት የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዴሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-A07934 የተሽከርካሪው አይነት ልዩ ጎታች የሻንሲ ቁጥር LZZ5CLVB9LA715592 ሞዴል ZZ4257V324HC1B የሞተር ቁጥር 201017740257 የሊብሬ ቁጥር 0270284 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 6/10/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም መሞስ ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-49739 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZTELMD7BJ050548 ሞዴል ZZ3255N3645B የሞተር ቁጥር WD615.69*111117011917* የሊብሬ ቁጥር 0245246 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 8/10/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዲስ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ኢ/ባ/ተ/ሎ/አ/ድ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-02-76564 የተሽከርካሪው አይነት ልዩ ጎታች የሻንሲ ቁጥር VF636MUAXFD000202 ሞዴል 36MUA1ENAN የሞተር ቁጥር DX113*525757* የሊብሬ ቁጥር 0104661 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 6/10/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አልባር ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-82019 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5BLSF2GN122598. ሞዴል ZZ1257S4641W የሞተር ቁጥር WD615.47-160107014117 የሊብሬ ቁጥር 0150175 ከላይ የተጠተሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 10/9/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ ት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**




# ጎበዙ የሒሳብ ተማሪና አሸናፊ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

እንደምን አላችሁ ልጆች፣ ሰላም ናችሁ? ሳምንቱ እንዴት ነበር፣ ጥሩ ነበር አይደል? ወይስ ሥራና ጥናት በዛባችሁ? ይህ ከሆነ አይከፋችሁ። ምክንያቱም እነዚህን ተግባራት መከወን ለነገ ተስፋችሁ ትልቅ ጥቅም አለው። ስኬታችሁ ላይም የሚያደርሳችሁ ነውና አትጥሉት። ልጆች ለመሆኑ ስለ አሸናፊነትና ውድድር ምን ያህል ታውቃላችሁ? በውድድር ተሳትፋችሁ አሸናፊ የሆናችሁበትን ቀን ታስታውሳላችሁ? እርግጠኛ ነኝ አዎ ብላችሁኛል። ጎበዝ ስለሆናችሁ ቢያንስ በትምህርት ቤት ተወዳድራችሁ ማሸነፋችሁ እንደማይቀር እገምታለሁ። ስለዚህም የአሸናፊነትን ስሜት ታውቁታላችሁ።

አሸናፊነት ምንድነው? ካላችሁ በራሱ ባህሪይ ነው። የምንለምደውና ሆነን የምንቀጥለው። የሚጀምረው ደግሞ ከአዎንታዊ አስተሳሰብ ሲሆን፤ ቀና ፣ በጎ ፣ ጥሩ ጥሩው የሚታይበት ብቻ ነው። ነገር ግን ሁልጊዜ በአዕምሯችን የሚመላለሰው አልችለውም የሚለው ከሆነ የማይበልጠን እንኳን ቢኖር አናሸንፍም። ምክንያቱም በእኔ አቅም አደረኩት አንልም። ውስጣዊ ደስታም አይኖረንም። ስለዚህም አሸናፊው መልካም ሃሳብ እንጂ ተግባሩ ብቻ አይደለም።

ልጆች አሸናፊ ለመሆን እና ለመባል ደግሞ ውድድር እንደሚያስፈልግ መቼም ታውቃላችሁ። እናም በምንወዳደርበት ጊዜ ውድድሩ ምን እንደሚያስፈልገው ቀድሞ ማወቅ ጠቃሚ ነው። በተጨማሪም ከማን ጋር መወዳደር እንዳለብንም ማወቅ ያስፈልጋል። ለዚህም ሁሌ አንባቢና ጠያቂ መሆን ግድ ነው። የአለመቻል ሥነልቦና በምንም መልኩ አዕምሯችን ውስጥ መቀመጥ የለበትም።

አሸናፊነት በዋነኛነት ትኩረቱን የሚያደርገው ከራሳችን ጋር መወዳደርን ነው። ሆኖም ውድድር ከሌለ ግን መበላለጥ አይመጣምና ከሌሎች ሰዎች ጋር መወዳደር ግድ ነው። አንዱ ደግሞ እንደእናንተ ያሉ ተማሪዎች የሚያደርጉት የትምህርት ውድድር ሲሆን፤ በምታስቆጥሩት ውጤት እንድትበልጡ ትሆናላችሁ። ስለዚህም አንደኛ ለመውጣት መወዳደር ይኖርባችኋል።

ልጆች በውድድር ውስጥ ያለ አሸናፊነት በርካታ ባህሪያት አሉት። የመጀመሪያው ባህሪው ልንደርስበት የምንፈልገውን ማወቅ ሲሆን፤ ለጉዳዩ የጠራ አመለካከት እንዲኖረን የሚረዳን ነው። የመጨረሻ መዳረሻ ግባችንን አስበን እንድንሰራም ያግዘናል። ሩቅ የምናስብም ያደርገናል።

ሌላው የአሸናፊነት ባህሪ ግብን ማስቀመጥና በእቅድ መመራት ሲሆን፤ ግባችንን ተግባራዊ ለማድረግ የተወሰነ ጊዜ፣ ሊለኩ የሚችሉ ተግባራትና ውጤት እንዲኖረን የሚያደርገው ነው። አዎንታዊ አመለካከቶች እንጂ ፍርሀት ጭንቀትንና ውጥረትን በውስጣችን እንዳናስተናግድ የሚያደርግም ባህሪ አለው። ቆራጥና ለነገሮች መሳካት ጠንክሮ መስራትም ሌላው ባህሪይው ነው። ራስን ማወቅም እንዲሁ። በዚህ ምድር አንድም ፍፁም ሰው የለም። ስለዚህም አሸናፊነት ፍፁምነት (ሁሉን አዋቂነት) አይደለምና ደካማና ጠንካራ ጎናችንን አውቀን ጎዶሏችንን እንድንሞላ የሚያደርገን ነው።

ልጆች ስለ አሸናፊነትና ውድድር ያነሳነው ያለምክንያት አይደለም። በሂሳብ ትምህርት እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር "በኢትዮ ማት ኦሎምፒያ "የተማሪዎች ውድድር ላይ ሁለት ዙሮችን አሸናፊ ሆኖ ሦስተኛውን ዙርም ለማሸነፍ እየተጣጣረ ስላለና የአሸናፊነትን ባህሪ ስለተላበሰው ተማሪ ልናወጋችሁ ፈልገን ነው። እንግዳችን ናታን ፍሬዘር ይባላል። የቤዛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነው። በትምህርቱ በጣም ጎበዝ አንደኝነቱን ማንም



ነጥቆት የማያውቅ ነው።

ናታን የመጀመሪያ ውድድሩን የጀመረው ከትምህርት ቤቱ ተመርጦ ሲሆን፤ ካሉ ጎበዝ ተማሪዎች ጋር ተወዳድሮ የላቀ ውጤት አምጥቷል። ያንን ካለፈ በኋላ ደግሞ ሁለተኛ ውድድሩን ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ላይ አድርጓል። እዚያም በከፍተኛ ውጤት ማሸነፍ ችሏል። ለዚህ ደግሞ ያበቃው ንባብ ወዳድነቱ ፤ ትምህርቱን በደንብ መከታተሉና የቤት ሥራውን ሳይሰራ ትምህርትቤት አለመሄዱ እንደሆነ ይናገራል።

ልጆች ናታን ገና የ 10 ዓመት ልጅ ቢሆንም ንባቡ አዳዲስ ነገሮችን እንዲሞክር ስለሚገፋፋው አልችለውም የሚለው ነገር የለም። በተለይ ፍላጎቱ የጠፈር ተመራማሪ መሆን ነውና ለዚያ የሚያበቃውን ነገር መሞከር በጣም ያስደስተዋል። ክረምትንም ቢሆን ትምህርት ስለሌለ በዚህ ሁኔታ እንደሚያሳልፍ ነግሮናል።

ናታን በጣም የሚገርመው ከትምህርቱ ጎን ለጎን ቤተሰቡን ያግዛል። ሳይታዘዝ ጭምር በጠዋት ተነስቶ ቤት ያስተካክላል። አልጋውንም የሚያነጥፈው ራሱ ነው። አሁን ግን ይህንን እገዛውን በመጠኑ ቀንሷል። ምክንያቱም ለሦስተኛ ዙር ፈተና መዘጋጀት አለበት። ፈተናው የሚሰጠው በኮከበፅብሃ ትምህርትቤት ሲሆን፤ ሁሉን ዝግጅት የተደረገው በኢትዮ ማት ኦሎምፒያ አማካኝነት እንደሆነ ነግሮናል።

ይህ ውድድር በጠቅላላ ስድስት ፈተናዎች ያሉበት ሲሆን፤ ናታን ሦስተኛውን ዙር ለመፈተን እየተዘጋጀ ነው። በስድስቱም አሸናፊ እንደሚሆን ያምናልም። ምክንያቱም ለዚያ የሚያበቃውን በቂ ዝግጅት እያደረገ ነው። የፈተናው ዋና ትኩረት ሒሳብ ላይ ቢሆንም አጠቃላይ ትምህርቱን በደንብ ማጥናትና የተሻለ ውጤት ማምጣት ካልተቻለ ማለፍ እንደማይችል ያውቃልና ለትምህርቱም ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

‹‹ አሸናፊነት በራስ መተማመንን ይሰጣል። የተሻለ ተማሪ ለመሆንም ያስችላል። ከሁሉም በላይ ሁልጊዜ አዲስ ነገርን ያስገኛል›› የሚለው ናታን፤ ተሸላሚና አሸናፊ ለመሆን የተገኙ እድሎችን መጠቀምና ልምዶቹን ቀምሮ ለሌላው ጊዜ መዘጋጀት ወሳኝ እንደሆነ ያነሳል። ሁልጊዜ አሸናፊነትን እያሰቡ መራመድም ተገቢ እንደሆነ ይመክራል። ልጆች እናንተው የናታንን ምክር ሰምታችሁ አሸናፊ ሁኑ፤ ነጋችሁንም አሳምሩ በማለት ለዛሬ አበቃን።

# ስፖርት





## የአፍሪካ እግር ኳስ ጠንሳሾች የዘመናት ልዩነት

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብፅ እኤአ 1957 የተጀመረውን የአፍሪካ ዋንጫ ጨዋታ የጠነሰሱና የጀመሩ አገራት በመሆናቸው ታሪክ ይዘክራቸዋል። እኤአ 1956 የኢትዮጵያ የግብፅና የሱዳን ባለሥልጣናት ከደቡብ አፍሪካ ተወካይ ጋር በመሆን የአፍሪካ አህጉራዊ ውድድርን ለመመስረት በፖርቹጋል በነበረው የፊፋ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ተገኙ። የመጀመሪያው የአፍሪካ ዋንጫም እኤአ 1957 በሱዳን መዲና ካርቱም እውን ሲሆን የደቡብ አፍሪካ ፌዴሬሽን ከተለያዩ ዘሮች የተውጣጣ ቡድን ለመላክ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከውድድሩ ተገለለ። ሶስቱ አገራት ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብጽ እየተፈራረቁ ሶስቱን የመጀመሪያ የአፍሪካ ዋንጫዎች በማንሳትም የአህጉሪቱ ሃያል ተፎካካሪ ሆኑ። ይሁን እንጂ የሶስቱ አገራት ሃያልነትና ብርቱ ተፎካካሪነት ዘመናትን የሚሻገር አልሆነም። ሁለቱ ምስራቅ አፍሪካውያን ጎረቤታሞች እንደ ታሪካቸው መራመድ ተስኗቸው ከሰሜን አፍሪካዋ አገር በብዙ ወደ ኋላ ቀሩ። ይህም የእግር ኳስ ደረጃ ልዩነት ዘመናትን ተሻገረ፡፡

ሌላው ቀርቶ ሶስቱ የአፍሪካ ዋንጫ ጠንሳሾች በአንድ የአፍሪካ ዋንጫ መድረክ ላይ ለመሳተፍ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ፈጅባቸው። ይህም ከ52 ዓመታት በኋላ ሦስቱ አገራት ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ አፍሪካ ዋንጫ መሳተፍ የቻሉበት ያለፈው የካሜሩን አፍሪካ ዋንጫን ታሪካዊ አደረገው።

በአፍሪካ ዋንጫ ቀዳሚ ስፍራ ያላቸው ሦስቱ አገራት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውን ዋንጫ አሸናፊ ቢሆኑም ግብፅ ሰባት ጊዜ በማሸነፍ ከየትኛውም አገር በላይ ክብረወሰንን ጨብጣለች። ሁለቱ የምስራቅ አፍሪካ አገራት ግን ዳግም ለዋንጫ ክብር መድረስ ቀርቶ ከሰሜን አፍሪካዋ አቻቸው ጋር ያላቸውን የእግር ኳስ ደረጃ ሰፊ ልዩነት ማጥበብ ሳይችሉ



ግብፅን ከ60 ዓመት በፊት በአፍሪካ ዋንጫ ፍፃሜ 4ለ2 የረታው ታሪካዊው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን፣

ዘመናት ነጉደዋል።

እግር ኳስ በምሥራቅ አፍሪካ አገራቱ ኢትዮጵያና ሱዳን ከፍተኛ ተወዳጅነት ያለውና ጥሩ ተሰጥኦ ያላቸው ተጫዋቾች መፍለቂያ እንደሆኑ ቢታመንም ከነበራቸው ከ1960ዎቹና 70ዎቹ ታላቅነት በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ኋላ ቀርተዋል። ከምሥራቅ አፍሪካ አገራት በብቸኝነት ዋንጫውን ያነሱት ኢትዮጵያና ሱዳን ተመሳሳይ የእግር ኳስ ታሪክን መጋራታቸው ለዚህ ልዩነት ምክንያት ይሆን?። ሁለቱ አገራት በአፍሪካ ዋንጫ ቀደምት ስፍራ ቢኖራቸውም ሁለቱም ብቸኛ ድሎቻቸውን ያሳኩት እራሳቸው አዘጋጅ በነበሩበት ውድድር ነበር። ኢትዮጵያ ለ31 ዓመታት ያህል ለአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያው ማለፍ አቅቷት እኤአ 2013 ነበር ወደ ውድድሩ መመለስ የቻለችው፤ በተመሳሳይ ሱዳንም ለ32 ዓመታት ያህል ከውድድሩ ርቃ እኤአ 2008 ነበር ተሳታፊ የሆነችው።

‹‹በእግር ኳሱ ዘርፍ ሱዳንና ኢትዮጵያን ወደ ኋላ በመመለስ ረገድ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሚና አላቸው›› የሚሉት የሚቺጋን ስቴት ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰርና 'አፍሪካን ሶከርስኬፕስ፡ ሀው ኤ ኮንቲነንት ቼንጅድ ዘ ወርልድ'ስ ጌም' የተሰኘ መጽሐፍ ደራሲ ፒተር አሌጊ ይናገራሉ። በሁለቱም አገራት የተራዘሙ የእርስ በርስ ጦርነቶች፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የኢኮኖሚ ውድቀትና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ተደማምረው በአገራቱ የእግር ኳስ እድገትና ሂደት ላይ የራሳቸውን ተጽዕኖ አሳድረዋል። የኢትዮጵያ እኤአ 1962 በተካሄደው በሦተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ያኔ አረብ ሪፐብሊክ ትባል የነበረችውን ግብፅ 4 ለ 2 በመርታት ቻምፒዮን በመሆን ድሏን አጣጣመች። ይህ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ወርቃማ ታሪክ ጥር 13/ 1954 ዓ.ም ሲፃፍ ግቦቹን ከመረብ ያሳረፉት ታሪካዊው ተጫዋቾች መንግሥቱ ወርቁ (ሁለት ግብ)፣ግርማ ተክሌና ኢታሎ ቫሳሎ አንዳንድ ግቦችን በስማቸው አስመዝግበዋል፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ኢትዮጵያ ፈርኦኖቹ ላይ ሁለትና ከዚያ በላይ ግብ አስቆጥራ ለማሸነፍ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ቆይታለች። ይህን ታሪክ ከስልሳ ዓመት በኋላ ለመቀልበስም ባለፈው እሁድ ከፈርኦኖች ጋር ያገናኛትን የ2023 የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታ ጠብቃለች፡፡ ዳዋ ሆጤሳና ሽመልስ በቀለም የስልሳ ዓመቱን የታሪክ ግንብ የናዱ ግቦችን በማስቆጠር ለምስራቅ አፍሪካ እግር ኳስ ትንሳዔ በር ሊከፍት የሚችል ታሪክ መስራት ቻሉ፡፡

ሱዳን እኤአ በ1970 እንደ አሊ ጋጋሪ፣ ጃክሳ በመባል የሚታወቀውና ናስር ኤዲንን ባካተተው ወርቃማ በሚባለው የእግር ኳስ ትውልዷ ጋናን 1 ለ 0 በመርታት ብቸኛውን ዋንጫ አሸንፋለች። ሱዳን በእግር ኳስ ታሪኳ ከኢትዮጵያ በተለየ መልኩ በተመሳሳይ ዓመት በሜክሲኮ በተካሄደው የዓለም ዋንጫ ላይ ለመሳተፍ ተቃርባም ነበር። ከሁለት ዓመት በኋላም እኤአ 1972 ሙኒክ ኦሊምፒክ ተሳትፋ በአንፃራዊነት የተሻለ የእግር ኳስ ታሪክ ጽፋለች። ነገርግን በቀጣዮቹ ዓመታት ‹‹ዘ ሴክሬታሪ በርድስ›› የተሰኘው ቡድኗ ውድቀት ገጠመው። ዛሬም ድረስ ከወደቀበት ለመነሳት ዳዴ እያለም ነው።

‹‹በወቅቱ አገሪቱ ውስጥ የነበረው መረጋጋት ለእግር ኳስ ማደግ ከፍተኛ ሚና ተጫውቶ ነበር። ነገር ግን የፖለቲካ አለመረጋጋት እና የምጣኔ ሀብት ችግሮች አገሪቱ በሌሎች ጉዳይ ላይ እንድታተኩር አድርጓታል›› በማለት የወርቃማው ትውልድ ቡድን አባል የነበረው በአሁኑ ወቅት የ77 ዓመት እድሜ አዛውንቱ ጃክሳ በቅርቡ ለቢቢሲ ተናግሯል።